በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥ እና አፈፃፀም በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ድርሞ (Executive Summery) vi
የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ራዕይ፣ ዓላማ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች 2
ራዕይ፡- 2
ዓላማ፡- 2
ተልዕኮ፡- 2
እሴቶች፡- 2
የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስልጣንና ተግባር፡- 3
የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል 5
ድርጅታዊ መዋቅር 5
የሰው ኃይል 5
የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ 5
የአሰራር ሥርዓት መግለጫ(process description) 6
የተቀናጀ የክፍያስርዓት / Integrated Billing System/ 6
ኤሌክትሮኒክ መንግስት አስተዳደር 7
የመንግስትና የግል ሽርክና (Public Private Partnership) 7
የኦዲቱ አላማ 8
የኦዲት አከባቢ (Potential Audit Area) 8
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) 9
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria) 9
ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 9
ክፍል ሁለት 12
ግኝቶች 12
የለሁሉ ኮንትራት አሠጣጥ ህግን የተከተለ፣ ውልን መሰረት ያደረገ እና የተሻለ አገልግሎት ለተጠቃሚው መስጠት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፤ 12
የለሁሉ ኮንትራት በመንግስት እና በግል ሽርክና ግዥ ለመፈፀም በጥናት መሰረት መሆኑን በተመለከተ 12
ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ ክፍያ ሥርዓት ግዥ አፈፃፀም በተመለከተ 14

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ጋር ያደረገውን ውል በግዥ ሰነዱ መሰረት መሆኑን በተመለከተ 15

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ጋር ያደረገውን ውል ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ 17

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ጋር የዋጋ ድርድር ማድረጉን በተመለከተ 18

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታ ከማውጣቱ በፊት አማካኝ የደንበኛ ብዛት እና የጨረታ መነሻ ዋጋ ጥናት ማድረጉን በተመለከተ 19

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የአማካሪ ድርጅት ቅጥርን በተመለከተ 21

በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ ወደ ለሁሉ አገልግሎት የሚገቡ አዲስ ተቋማትን በተመለከተ 22

የለሁሉ ኮንትራት አፈጻጸም የአገልግሎቱን በደንበኞች የስምምነት ሰነድ (service level aggrement) መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን መገምገም፣ 25

በጨረታ ያሸነፈው ድርጅት ውል ላይ በተቀመጠው ቀን መሰረት አገልግሎት መስጠት መጀመሩን በተመለከተ 25

አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት እና የአገልግሎት ተቋማቱ የፋይናንስ ሥርዓት አተገባበር በተመለከተ 26

ሠንጠረዥ 1፡በለሁሉ ኮንትራት ሊሰበሰብ የታቀደ እና የተሰበሰበ ገንዘብ ልዩነት 28

በተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) አስተዳደር በተመለከተ 30

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ሥርዓቱን ለመከታተል የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ 31

ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅትን የፋይናንስ ኦዲት ማድረጉን በተመለከተ 34

ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላትን ማቅረቡን በተመለከተ 34

የለሁሉ አገልግሎት መስጫ የቀረቡ ቢሮዎች በተመለከተ 36

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቀረጥ ነፃ የገቡ ንብረቶች አያያዝን በተመለከተ 37

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት ሲስተም ኦዲት ማስደረጉን በተመለከተ 39

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት አፈፃፀምን በተመለከተ 41

ክፍል ሶስት 49

መደምደሚያ 49

ክፍል አራት 52

የማሻሻያ ሀሳቦች 52
አባሪ 1 i

ድርሞ (Executive Summery)

አሁን በደረስንበት ጊዜ ላይ በግለሰብ ህይወት ይሁን በአጠቃላይ ሀገራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎች የሚጫወቱት ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ቴክኖሎጂው በየትኛውም የአለማችን ጫፍ የሚገኙ ሰዎችን እና ሀገራትን በማቀራረብ መረጃዎችን በማለዋወጥ አለምን ወደ አንድ መንደርነት እየለወጠ ይገኛል፡፡ ተግባራትንና አገልግሎትን በማዘመንና በማላቅም ድርሻው የገዘፈ ነው፡፡ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርም ሀገሪቱ በምታደርገው ሁሉን አቀፍ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎች የማይተካ ሚናቸውን እንዲወጡ ዘርፉን እንዲመራ ታስቦ የተቋቋመ ሚኒስቴር መ/ቤት ነው፡፡ ከእነዚህ ሥራዎች ውስጥ የኤሌክትሮኒክስ መንግስት /E-governmene/ አንዱ ነው፡፡ የኤሌክትሮንክስ መንግስት በውስጡ የተለያዩ አገልግሎቶችን የያዘ ሲሆን ከእነዚህ አገልግሎቶች አንዱ የለሁሉ አገልግሎት ነው፡፡በዚሁ መሰረት በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን በመንግስት እና በግል ሽርክና (Public Private partnership PPP) ግዥ ለመፈፀም ያስፈለገበትን አግባብ ማለትም (በመንግስት ሊሰጥ ስላለመቻሉ፣ በግል ቢሰጥ ስለሚያስገኘው ጥቅም ወዘተ) በጥናት መሰረት ስለመወሰኑ፣ እንዲሁም የለሁሉ ኮንትራትን ለግል ሴክተር ለጨረታ ከማቅረቡ በፊት በመንግስት ተቋማት አገልግሎቱን መስጠት እንደማይቻል የተረጋገጠ ስለመሆኑ ማስረጃው ለኦዲት አልቀረበም፡፡
- እንዲሁም ለግል ሴክተር ከመቅረቡ በፊት በመንግስት መ/ቤቶች ማለትም (እንደ ባንክ፣ ፖስታ ቤት ወዘተ) አገልግሎቱን መስጠት እንዲችሉ ባለመደረጉ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡
    - የመንግስት እና የግል ሽርክና በባህሪው ከመንግስትና በግል ባለሀብቱ (ኮንሴሽነሩ) መካከል የሚደረግ ሽርክና በመሆኑ አገልግሎቱ በMonopoly በግል ሴክተሩ ብቻ እንዲያዝ ከማድረጉም በላይ የለሁሉ አገልግሎት (service based) በመሆኑ ሌሎች የክፍያ አማራጮች ለመጠቀምና አገልግሎቱን ማሳደግ ያልተቻለ መሆኑ፣
    - አገልግሎቱ ለለሁሉ ሴንተር ተብለው በተከፈቱ 34 ማእከሎች ብቻ መውሰኑ የተፈለገውን አገልግሎት ማቅረብ አልተቻለም፡፡ ነገር ግን ይህ አገልግሎት ለምሳሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚሰጥ ቢሆን በአዲስ አበባ በተለያዩ ቦታዎች ባሉ 422 ቅርንጫፎች፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት የሚሰጥባቸው 180 ቢሮዎች

አገልግሎቱን በመስጠት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ከመሆንም አልፎ የአገር ሀብት (resorce) በአንድነት ለተለያዩ አገልግሎቶች መጠቀም ያልተቻለ መሆኑ፤

- የለሁሉ አገልግሎት የሚሰጥባቸው የክፍያ ማእከላት ኪራይ በተገልጋይ ተቋማት(utilities) ስለሚሸፈን ተጨማሪ ወጪ እያስከተለባቸው መሆኑ፤
- ከ ብር 5000 በላይ የሚከፍሉ ደንበኞች ከባንክ ሲፒኦ አሰርተው የሚከፍሉበት አሰራር መኖሩ ይህም ደንበኞች የሲፒኦ ማሰሪያ ከብር 25 እስከ ብር 50 ተጨማሪ እንዲከፍሉ ማድረጉ፤ በተጨማሪም የሲፒኦ ክላሪቲ እስከ 15 ቀን እንደሚቆይ እና ይህም ገንዘቡ በውሉ መሰረት ለተገልጋይ ተቋማት(utilities) በ48 ሰአት ሳይገባ እንዲዘገይ ማድረጉ ታውቋል፡፡

➢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት በሀገሪቱ ሊኖር ስለሚችለው የተቀናጀ ክፍያ ስርዓትን የተመለከተ የአዋጭነት ጥናት ያላጠና መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም የአገልግሎቱ ባለቤት የሆኑት የተገልጋይ ተቋማት(utilities) የፍላጎት መግለጫ (Need assessment) አለመስራቱ ታውቋል፡፡

➢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ያደረገው ውል ከግዥ ሰነዱ (Request for proposal (RFP)) መሰረት ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

- በኤክስፕረሽን ኦፍ ኢንተረስት ለተመረጡ ድርጅቶች በተላከው ሌተር ኦፍ ኢንቫይቴሽን RFP ላይ ይህ ኢንቫይቴሽን አይተላለፍም ተብሎ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን በኮንትራት ሰነዱ አንቀጽ 24 ላይ ውሉ ለሰብሲደሪ ወይም አሶሼት ካምፓኒ እንዲተላለፍ የተፈቀደ መሆኑ፣
- በዚህም መሰረት ጨረታውን ያሸነፈው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር እ.አ.አ ሀምሌ 5 2011 ቁጥር UBS/0005/2011 በተጻፈ ደብዳቤ ኮንትራት አሳይመንት ለክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር ስራውን ያስተላለፈ መሆኑን እና ይህም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደ መሆኑ፣
- ሌተር ኦፍ ኢንቫይቴሽን ላይ በተቀመጠው መሰረት ውል ያልተዘጋጀ እና ያልተፈረመ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር ሰብሲደሪ ወይም አሶሼት ካምፓኒ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ያላቀረበ መሆኑ፤

- ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶልሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በክፍያ ፋይናንሽያል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር ውስጥ ምንም አይነት ባለቤትነት ድርሻ እንደሌለው ከድርጅቶቹ መመስረቻ ጽሁፍ ለማወቅ ተችላል፤
- በተጨማሪም ክፍያ ፋይናንሽያል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር የተቋቋመው እ.አ.አ የካቲት 2010 ሲሆን የኮንትራት አሳይመንቱን ሲቀበል በጨረታው የሚጠይቀውን 5 ዓመት የስራ ልምድ እና ቢያንስ 4 የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ የሰራ የሚሉትን መስፈርቶች የማያሟላ ሆኖ ሳለ ኮንትራቱ ሙሉ በሙሉ ተላልፎ እንዲሰራ መደረጉ ታውቋል፡፡

➢ በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 45 ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ በተጠቀሰው መሰረት ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸም ግዥ ካልሆነ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ባቀረበው ዋጋ እና ከዋጋ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የመንግስት መ/ቤት ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ድርድር ማድረግ እንደማይቻል ተገልፆል፡፡ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት (unified billing system (UBS 1)) አሸናፊው ድርጅት ከግሎባል ኮምፒቲንግ ሶልሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ለUBS 1 ያቀረበው ዋጋ ብር 1.43 ቢሆንም በኮንትራት ሰነዱ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከድርጅቱ ጋር ድርድር በማድረግ የተዋዋለው ዋጋ በብር 2.56 ቫትን ሳይጨምር መሆኑ፣ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችለዋል፡፡

➢ በተጨማሪም በውሉ መሰረት ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) በብር 1.13 እንዲጨምር በማድረግ በአጠቃላይ ከተቋማቱ የሚጠበቀው የደንበኛ ወርሃዊ የትራንዛክሽን ብዛት በአማካኝ 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺ) አካባቢ ሲሆን ለተገልጋይ ተቋማት (utilities) በወር 1,017,000 ብር ማለትም በዓመት 12,204,000 ብር ሲሆን ለሁሉ ከተጀመረበት የካቲት 2005 ዓ.ም እስከ ህዳር 2011 ዓ.ም ድረስ ማለትም የ5 ዓመት ከ 9 ወር 70,173,000 ብር ተጨማሪ የኮሚሽን ክፍያ አስከትሏል፡፡

➢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን ግዢ ለ[(unified billing system (UBS 1 እና UBS 2)] ጨረታ ከመውጣቱ በፊት የጨረታ መነሻ ዋጋ (Estimated price) ሳይቀመጥ መከናወኑ እና በዚሁ ጨረታ ላይ ለፋይናንሻል ውድድር አንድ ተጫራች ብቻ ያለፈ ሲሆን ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ ጨረታውን እንዲያሸንፍ መደረጉ ታውቋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ያደረገው ውል መሰረት ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የሚሰበስቡትን የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀሙ ሲገመገም እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡
  - የአዲስ አበባ ውሃ እና ፍሳሽ ባለስልጣን ለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት የካቲት ከ2005 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 2010 ዓ.ም (ከ5 ዓመት በላይ) እንዲሰበሰብለት የላከው ዳታ የገንዘብ መጠን ብር 6,472, 048,746.9 ሲሆን የተሰበሰበው ብር 3,198,033,890.00 (49.4%) መሆኑን፤
  - የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በአዲስ አበባ በለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት ከጥር 2005 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2010 ዓ.ም ድረስ እንዲሰበሰብለት የላከው ዳታ የገንዘብ መጠን ብር 6,318,693,418.68 ሲሆን የተሰበሰበው ብር 3,879,997,662.74 (61%) መሆኑን
  - የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በመቀሌ እና ባህርዳር በለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት ከየካቲት 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2010 ዓ.ም ድረስ እንዲሰበሰብለት የላከው ዳታ የገንዘብ መጠን ብር 488,227,105.02 ሲሆን የተሰበሰበው ብር 246,537,910.52 (50.4%) መሆኑን ታውቋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ከግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ባደረገው ውል መሰረት የፋይናንስና የክፍያ ሥርዓቱን የሚከታተልበት ስርአት ስለመዘርጋቱ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ታይተዋል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በUBS 1&2 ውል አባሪ 8 ገጽ 2 መሰረት፡-
  - security Deposit እንደ ማስተማማኛ እንዲቀመጥ ይህም በየጊዜው ዝቅተኛ ባላንስ መጠኑ እንዳይጎድል ማሻሻያ የሚደረግበት ለእያንዳንዱ UBS 1&2 ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ) እንዲሆን እንዲሁም ቅጣቶች በሚኖርበት ጊዜ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየወሩ ከተቀመጠው ገንዘብ እንደሚቀንስ የተገለፀ ቢሆንም በውሉ መሰረት ተግባራዊ አለመሆኑ፤
  - ለUBS 1 የስራ አፈጻጸም ዋስትና(Performance guarantee in opretion period) ብር 1,800,000 ከግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ኮንትራቱን እስኪጨርስ ድረስ ክትትል እየተደረገ መታደስ እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም አለመደረጉ፤

- ለUBS 2 የስራ ማስፈፀሚያ ዋስትና(Performance guarantee in opretion period) ብር 2,200,000 ከግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ኮንትራቱን እስኪጨርስ ድረስ ክትትል እየተደረገ መታደስ እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም አለመደረጉ ታውቋል፡፡

➢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት በገለልተኛ አካል ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ሲስተም ሶፍትዌር ኦዲት (system audit) በማካሄድ ከሲስተሙ የሚወጣው ሪፖርት ትክክለኛነት ማረጋገጥ ቢኖርበትም ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

➢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶች በአንድ ቦታ እንዲገኙ (one stop shop) በማድረግ የተቀናጀ የክፍያ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ታይቷል፡-

- በUBS1 እና በUBS2 በተደረገው ውል መሰረት በአዲስ አበባ፣መቀሌ እና በባህርዳር ከተሞች ማህበረሰቡ የተለያዩ ክፍያዎችን (ውሃ፣መብራት፣ስልክ) በአንድ ቦታ እንዲከፈል እና ማህበረሰቡ እንዲጠቀም ለማስቻል ሲባል የተዘረጋ ቢሆንም ኢትዮ ቴሌኮም ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች፣ ኢንባሲዎች እና ሌሎች ትልልቅ ተቋማትን የሚያስከፍለው በቴሌ ሾፕ መሆኑ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከፍተኛ ሀይል ተጠቃሚ ደንበኞችን ኢንዱስትሪዎችን፣ ትላልቅ ተቋማትን እና የቅድመ ክፍያ ቆጣሪዎች አገልግሎት በራሱ ደንበኞች አገልግሎት እንደሚያስከፍል መሆኑ፤
- እንዲሁም በUBS2 ውል መሰረት አዋሳ፣ አዳማ፣ መቀሌ እና በባህርዳር ከተሞች (ውሃ፣መብራት፣ስልክ) በተቀናጀ መልኩ አገልግሎት ለመስጠት ቢዋዋልም፤ አገልግሎቱ በአዋሳ እና አዳማ ከተሞች አለመጀመሩ፤ በተጨማሪም በመቐለ እና በባህርዳር ከተሞች የውሃ ክፍያ የአገልግሎት በለሁሉ የክፍያ ማዕከል የማይከፈል መሆኑ የታቀደው የአንድ መስኮት አገልግሎት አለመተግበሩ ታውቋል፡፡

➢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና ከማህበረሰቡ የደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት ያላደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም በአገልግሎት ወቅት የሚፈጠሩ ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚያስችል ስርአት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

መግቢያ

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን ልማት አስፈላጊነት በመገንዘብና በሃገሪቱ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የዲሞክራሲ ፣ የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ፣ የልማትና የሰላም መጠናከርን እንዲያግዝ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲን በአዋጅ ቁጥር 360/1995 በማቋቋም አያሌ ሥራዎች ተከናውነዋል ፡፡

2. መንግስት በሀገሪቱ የሚገኙ መንግስታዊ መ/ቤቶች ከተቋቋሙበት ዓላማ አኳያ ተቋማዊ ለውጥ በሚያመጡበትና አሠራራቸውን በማሻሻል ውጤታማና ፈጣን ለውጥ በሚያስመዘግቡበት ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫ ላይ በማተኮር የለውጡ ተዋናዮች እንዲሆኑ የተለያዩ የዕድገትና የለውጥ እርምጃዎችን በፖሊሲ ደረጃ በመቅረጽ ለተግባራዊነታቸው ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

3. በመሆኑም የዘርፉን መሠረተ ልማት በማስፋፋት ከዓለም ጋር ተወዳዳሪ ለመሆንና ቀልጣፋ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ በዘርፉ ተቋማት ላይ በተደረገ የሥልጣንና ተግባር ቅኝት መሠረት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ልማት ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ እና በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሥር የነበሩት የመገናኛ ዘርፍ ሥራዎች በአንድነት ተደራጅተው መመራቱ አስፈሊጊ ሆኖ በመገኘቱ እነዚህን ተቋማት በማዋሃድ የኢትዮጵያ ፌዳራሊዊ ዳሞክራሲያዊ ሪፑብሉክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሠረት የመገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተቋቋመ ሲሆን በድጋሚ የኢትዮጵያ ፌዳራሊዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሉክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም በድጋሚ ተቋቁሟል፡፡ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና መገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በማዋሃድ የኢትዮጵያ ፌዳራሊዊ ዳሞክራሲያዊ ሪፑብሉክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 ዓ.ም መሠረት ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በሚል አዲስ ሚኒስቴር ተቋቁሟል፡፡

4. አሁን በደረስንበት ጊዜ ላይ በግለሰብ ህይወት ይሁን በአጠቃላይ ሀገራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎች የሚጫወቱት ሚና እጅግ

ከፍተኛ ነው፡፡ ቴክኖሎጂው በየትኛውም የአለማችን ጫፍ የሚገኙ ሰዎችንና ሀገራትን በማቀራረብና መረጃዎችን በማለዋወጥ አለምን ወደ አንድ መንደርነት እየለወጠ ይገኛል፡፡ ተግባራትንና አገልግሎትን በማዘመንና በማላቅም ድርሻው የገዘፈ ነው፡፡ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርም ሀገሪቱ በምታደርገው ሁሉን አቀፍ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎች የማይተካ ሚናቸውን እንዲወጡ ዘርፉን እንዲመራ ታስቦ የተቋቋመ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ነው፡፡ ከእነዚህ ሥራዎች ውስጥ የኤሌክትሮኒክስ መንግስት /E-Government/ አንዱ ነው፡፡ የኤሌክትሮንክስ መንግስት በውስጡ የተለያዩ አገልግሎቶችን የያዘ ሲሆን ከእነዚህ አገልግሎቶች አንዱ የለሁሉ አገልግሎት ነው፡፡

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ራዕይ፣ ዓላማ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች

ራዕይ፡-

5. የሁሉም ኢትዮጵያዊ ስራና ህይወት በመረጃና በመገናኛ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሆኖ ማየት

ዓላማ፡-

6. የመረጃ እና መገናኛ ቴክኖሎጂ ዘርፍን በማሳደግና በፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን አስተዋፅኦ በማጎልበት ሀገሪቱ የፈጣን ልማትና እድገት ተጠቃሚ እንድትሆን ማድረግ

ተልዕኮ፡-

7. መረጃና ቴክኖሎጂ በማልማት እና በሁሉም ስፍራ በስፋት በመጠቀም የህብረተሰቡን ኑሮ ማሻሻል እና መገናኛ ቴክኖሎጂ ለአገሪቱ እድገት የሚሰጠውን ድጋፍ ማሳደግ

እሴቶች፡-

8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ እሴቶች ሰራተኞቻችን ለውጤታማነታችን መሰረቶች ናቸው፣

- ለደንበኞች እርካታ ቅድሚያ መስጠት፣
- የዜጎችን ተሳትፎ ማጎልበት፣
- ለመልካም አስተዳደርና ለዲሞክራሲ ግንባታ አጋርነትን ማረጋገጥ፣
- ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር መራመድ፣
- በቡድን የመስራት መንፈስን ማስፈን፣

- የግልፅነት፣የተጠያቂነትና አሳታፊነትን መርህ ማስፈን፣
- አዳዲስና አግባብነት ያላቸው እውቀቶችንና አሰራሮችን በማፈላለግ ጥቅም ላይ ማዋል ናቸው፡፡

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስልጣንና ተግባር፡-

9. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 መገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከታች የተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባር የነበረው ሲሆን በ2011 አዲስ በተደረገው የሚኒስቴር መስሪያ ቤት አወቃቀር አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቀድሞው ሳይንስና ቴክኖሎ ሚኒስቴር ጋር በመዋሃድ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተብሎ በድጋሚ ተቋቁሟል፡፡ የመገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የነበረ ጊዜ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካከል፡-

- የመገናኛ አገልግሎቶችና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
- የመገናኛ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት ፖሊሲን በብቃት ለማስፈፀም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም እንዲገነባ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- የመገናኛ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና አስተማማኝነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ደረጃዎችን ይወስናል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፤
- ለቴሌ ኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች የሚጠየቀውን ክፍያ ይቆጣጠራል ፤
- የቴሌ ኮሚኒኬሽንና የፖስታ አገልግሎቶች በመስጠት ስራ ላይ ለሚሰማሩ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤
- ለቴሌ ኮሚኒኬሽን አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ያረጋግጣል፤
- በመንግስታዊ ተቋማት የመረጃ ስርዓትን ከመገንባትና ከማቀናጀት አንፃር የመንግስት የዶሜን ስም ይደለድላል፤ አድራሻ ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፤
- የሀገሪቱን የከፍተኛውን ደረጃ መለያ ዶሜይን ስም ሀገራዊ የአስተዳደር ስርዓት እንዲፈጠርና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚመለከታቸውን ያስተባብራል፣ ለአፈፃፀሙም እገዛ ያደርጋል፤
- መረጃ በተፋጠነ መልክና በተመጣጠነ ወጪ ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

- በፌደራልና በክልል መንግስታት ተቋማት መካከል እንዲሁም በፌደራልም ሆነ በክልል ተቋማት ውስጥ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን መረብ መዘርጋቱን ይከታተላል፣ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤
- ለህዝብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያተኮሩ መሰረታው ሲስተሞችና አገልግሎቶች በኮንፒተር የተደገፉ እንዲሆኑና ደረጃ በደረጃም ለተጠቃሚዎች በቀጥታ አገልግሎት ሊሰጡ በሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸታቸውን ያረጋግጣል፤
- በስራ ላይ የሚውሉ የኮንፒተር መረቦችና አፕሊኬሽኖች ከቴክኒክና አሰራር አኳያ መቀናጀትና መናበብ መቻላቸውን ያረጋግጣል፤
- በመንግስታዊ ተቋማት መካከል የተቀናጀና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ፍሰትና ልውውጥ እንዲኖር ድጋፍ ይሰጣል፤ በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋሉ ይከታተላል፤
- በሌሎች የመንግስት አካላት ብቃታቸው ለማይረጋገጥ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎችና ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
- የቴሌ ኮሚኒኬሽን፣ የፖስታ እና የኢፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን ለመቆጣጣር አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ያወጣል፤
- በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኒሎጂ ዘርፍ የሚሰጥ ትምህርት እንዲስፋፋ ከትምህርት ተቋሞች ጋር ይተባበራል፤
- በመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማትን ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል የስልጠናና የፕሮጅክት አስተዳደር እና አፈፃፀም ምክክር ይሰጣል፤ መመሪያ ያወጣል ስለአፈፃፀሙ ክትትል ያደርጋል፤
- የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ እንድያድግ ምቹ ሁኔታዎችን ይቀይሳል ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- ለኢትዮጵያ የተመደበውን የሬድዮ ፍሪኩዌንሲ አጠቃቀም ይፈቅዳል ይቆጣጠራል፤
- ብሄራዊ የቴሌ ኮሙኒኬሽን ቁጥር ፕላን ያወጣል ቁጥሮችን ይመድባል፣ ያስተዳድራል እንዲሁም አጠቃቀማቸውን ይቆጣጠራል፤
- ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚኒስተሮች ምክር ቤት በሚያፀድቀው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያዎች ያስከፍላል የሚሉ ናቸው፡፡

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል

ድርጅታዊ መዋቅር

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአንድ ሚኒስትር እና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች የሚመራ ሲሆን፣ በሁለት ዘርፎች ማለትም የልማት እና ሬጉላቶሪ ዘርፎች ያሉት ሲሆን ለልማት ዘርፉ ተጠሪ የሆኑ ስምንት ዳይሬክቶሬቶች ያሉ ሲሆን፤ በሬጉላቶሪ ዘርፉ ስድስት ዳይሬክቶሬቶች እና አንድ ጽ/ቤት በድምሩ አስራ አራት ዳይሬክቶሬቶችና አንድ ጽ/ቤት የተዋቀረ ነው፡፡ እንዲሁም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሬጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዴኤታ ተጠሪ የሆኑ ሁለትተቋማት ማለትም የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ፖስታ አገልግሎት ድርጅት የሚቆጣጠር ነው፡፡

የሰው ኃይል

11. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህዳር ወር 2011 ዓ.ም ከቀረበው ማስረጃ ለማወቅ እንደተቻለው 120 (43.6%) ሴት ሰራተኞች፣ 155 (56.4%) ወንድ ሰራተኞች በድምሩ 275 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን ሰራተኞች የሰው ኃይል ባላቸው የሙያ ደረጃ ሲተነተን ማስተርስ 25 (9%) የመጀመሪያ ዲግሪ 155 (56.4%)፣ ዲፕሎማ 19 (6.9%) እና ከዲፕሎማ በታች ያሉ 76 (27.6%) ናቸው፡፡

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

12. የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ስራውን የሚያከናውነው በመንግስት በሚመደብለት በጀት ሲሆን በ2008፤ በ2009 እና 2010 በጀት ዓመታት እንደየ ቅደም ተከተሉ ከመንግስት የተመደበለት መደበኛ እና ካፒታል በጀት ብር285,303,400.00፤ ብር437,453,530.00 እና ብር 534,110,650.00 ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ2008 በጀት ዓመት ብር 218,747,000.00፤ በ2009 በጀት አመት ብር 321,763,111.00 እንዲሁም በ 2010 በጀት ዓመት ደግሞ ብር 207,282,751.79 ስራ ላይ አውሏል፡፡

ዓ.ም	የተመደበ በጀት		ጠቅላላ የተመደበ በጀት	ጥቅም ላይ የዋለ		ጥቅም ላይ የዋለ ጠቅላላ ወጪ	
	መደበኛ	ካፒታል		መደበኛ	ካፒታል	በብር	በፐርሰንት
2008	65,717,400	219,586,000	285,303,400	53,855,000	164,892,000	218,747,000	77 %
2009	75,403,530	362,050,000	437,453,530	57,151,689	264,611,422	321,763,111	74 %
2010	89,500,850	444,609,800	534,110,650	66968163.46	140314588.33	207282751.79	39 %

የአሰራር ሥርዓት መግለጫ(process description)

የተቀናጀ የክፍያስርዓት / Integrated Billing System/

13. የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት ማለት በተለያዩ የመንግስት ተቋማት የሚሰበሰቡ ክፍያዎችን በማቀናጀት ሁሉንም ክፍያዎች በአንድ ቦታ እንዲከፈሉ ማድረግ ነው፡፡ይህም አገልግሎቱን ከማዘመን በተጨማሪ ህብረተሰቡ ጊዜውን እንዲቆጥብ እና አላስፈላጊ ወጪ እንዳያወጣ ያደርጋል፡፡

14. በሀገራችን የለሁሉ አገልግሎት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ አገልግሎቱን ከሶስት የመንግስት ተገልጋይ ተቋማትማለትም ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ አገልግሎት እና ኢትዮ ቴሌኮም ውል በማሰር ስራው እየተሰራ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን አገልግቶት ድርጅት በ2007 ዓ.ም ወደ ለሁሉ አገልግሎት ገብቶ በ2009 ዓ.ም ውል የተቋረጠ መሆኑን እና የትራፊክ ቅጣት ክፍያ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ለሁሉ አገልግሎት ተጨምሯል፡፡ በተጨማሪም በ2006 ዓ.ም በአራት ክልል ከተሞች (መቀሌ፣ባህር ዳር፣አዳማ እና ሃዋሳ) አገልግሎቱ ከሶስት የመንግስት ተገልጋይ

ተቋማትውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኮርፖሬሽን እና ኢትዮ ቴሌኮም ውል በማሰር ስራው እየተሰራ ይገኛል፡፡

15. የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓትን ለመንግስትና ግል ሽርክና/puplic private partnership/ ለግል ሴክተሩ አገልግሎት ላይ የተመሰረተ ፕሮጀክት (service oriented project) ሆኖ የግል ሴክተሩ ከሚሰጠው አገልግሎት ከተቋማቱ ኮሚሽን በመሰብሰብ አገልግሎት እንዲሰጥ አድርጓል፡፡ በዚህም በጨረታ ያሸነፈው ድርጅት (ከግሎባል ኮምፒቲነግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር) ጋር ለአዲስ አበባ(UBS 1) እና ለአራት ክልል ከተሞች (መቀሌ፣ባህር ዳር፣አዳማ እና ሃዋሳ(UBS 2)) ውል በማሰር በክፊል አገልግሎቱ እየሰጠ ይገኛል፡፡

ኤሌክትሮኒክ መንግስት አስተዳደር

16. ኤሌክትሮኒክ መንግስት አስተዳደር ማለት በመንግስት የሚሰጡ አገልግሎቶችን የኢንፎርሜሽንና መገናኛ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ማቅረብ ሲሆን መንግስት ከተገልጋዮች፣ መንግስት ከንግዱ ማህበረሰብ እና መንግስት ከመንግስት የሚደረጉ ግንኙነቶችን ይጨምራል፡፡ኤሌክትሮኒክ መንግስት አስተዳደር ዓላማ የኤሌክትሮኒክ መንግስት አስተዳደር ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ እና በመጠቀም የህዝብ አስተዳደርና አገልግሎት ዘመናዊ በማድረግ ውጤታማና ብቃት ያለው የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግ ነው፡፡

የመንግስትና የግል ሽርክና (Public Private Partnership)

17. የመንግስትና የግል ሽርክና (Public Private Partnership) ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት እና በግል ባለሀብት መካከል በሚደረግ ውል በግሉ ባለሀብት ተሳትፎ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ሲሆን ኮንሴሽነር ተብሎ የሚታወቀው የግል ባለሀብት፡-

ሀ/የግንባታ ፕሮጀክቶችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በኮንሰሽን ኪራይ የሚሰጡ ስራዎችን ለማከናወን ግዴታ የሚገባበት፣

ለ/የመንግስት ተግባር የሆኑ ስራዎችን ከማከናወን ወይም የመንግስትን ንብረት ስራ ላይ ከማዋል ጋር በተያያዘ በፋይናንስ፣ በቴክኒክና በስራ እንቅስቃሴ ረገድ የሚኖሩ ኃላፊነቶችን በአመዛኙ የሚወስድበት፤

ሐ/የመንግስት ተግባር የሆኑ ስራዎችን በማከናወን ወይም የመንግስትን ንብረት ስራ ላይ በማዋል ለሚሰጠው አገልግሎቶች ከመንግስት ክፍያ የሚያገኝበት ወይም በተጠቃሚዎች ላይ ከሚጣል ክፍያ ገቢ የሚሰበስብበት ወይም በሁለቱም መንገዶች ለአገልግሎቱ ክፍያ የሚያገኝበት ውል ነው፡፡

18. የለሁሉ አገልግሎት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ የጋራ ትብብር በለሁሉ ማእከላት አሰራር ለማበልጸግ/Build/፣ ለማስተዳደር/operate/ በመጨረሻም ለባለቤቱ ለማስረከብ/transfer/ የተደረገ የስምምነት ውል ነው፡፡ በመጀመሪያ የአንድ መስኮት የተቀናጀ የክፍያ አገልግሎት ስርአት ሲዘረጋ በመነሻነት ዋነኞቹ 3 አገልግሎት ሰጪዎች ማለትም ውሃ፣ መብራት እና ስልክ በተለያየ ቦታ እና ጊዜ የሚሰጡትን አገልግሎት ወደ አንድ መስኮት ማምጣት ሲሆን በቀጣይም ተመሳሳይ ከመንግስት ወደ ህብረተሰብ የሚደርሱ አገልግሎቶችን ማካተት በሚያስችል መልኩ እና አገልግሎቱን ለደንበኞቹ ምቹ ጊዜን ቆጣቢ እና ተደራሽ ለማድረግ እንዲያስችል ተደርጎ የተዘረጋ ነው፡፡

የኦዲቱ አላማ

19. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥና አፈፃፀም መገምገም የሚል ነው፡፡ እንዲሁም የለሁሉ ኮንትራት አፈፃፀምን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ከተገልጋይ ተቋማት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በመገምገም አፈፃፀሙ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ አጥጋቢ ያልሆነበትን ምክንያቶች ለይቶ በማውጣት የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

የኦዲት አከባቢ (Potential Audit Area)

20. ለክዋኔ ኦዲቱ የጠመረጠው የኦዲት አካባቢ (በለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥና አፈፃፀም በተመለከተ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም) የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

21. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ስር ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተለይተዋል፡፡ እነርሱም-

1. የለሁሉ ኮንትራት አሠጣጥ የግዥ ህጉን የተከተለ፣ ውልን መሰረት ያደረገ እና የተሻሻለ አገልግሎት ለተጠቃሚው መስጠት በሚያስችል መልኩ ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መልኩ የተከናወነ መሆኑን መገምገም፣

2. የለሁሉ ኮንትራት አፈጻጸም የአገልግሎቱን በደንበኞች የስምምነት ሰነድ (service level aggrement) መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን መገምገም፣

3. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለለሁል አገልግሎት የሚያደርገውን ድጋፍ ክትትል፣ የመረጃ ልውውጥና የመረጃ አያያዝ እና ቅንጅታዊ አሰራርን መገምገም ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria)

22. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን (Audit Issue) ለመመዘን የሚረዱ 30 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

23. ዝርዝር ኦዲቱ የሚሸፍነው ኦዲቱ የለሁሉ አገልግሎት ኮንትራት ግዢ ከተጀመረበት 2002 ዓ.ም ኦዲቱ እስኪጠናቀቅ ያለውን ጊዜ ሲሆን ኦዲቱን በዋናነት የተከናወነው በሚኒስተር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ ከለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥና አፈፃፀም ጋር የተያያዙ ማስረጃዎችን በመከለስ፣ ከባለድርሻ አካላት፣ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና አገልግሎት ሰጪ አካላት መረጃዎችን መሰብሰብ ማለትም ከኢትዮ ቴሌኮም ፣ የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ አገልግሎት ፣ የአዲስ አበባ ውሃ እና ፈሳሽ ባለስልጣን ፣የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኢጀንሲ ፣የኢትዮጵያ ብሮድካስቲነግ ኮርፖሬሽን እንዲሁም የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት

እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ተያያዥ መረጃዎችን በመከለስ መረጃው ተሰብስበዋል፡፡

24. እንዲሁም ለግሎባል ኮምፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ ማህበር እና ለክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ተያያዥ መረጃዎችን በመከለስ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በተጨማሪም በናሙና የተመረጡ 17 የክፍያ ማዕከላት ማለትም (ቤቴል፣ አጠና ተራ፣ ኮልፌ፣ አየር ጤና፣ አራት ኪሎ፣ ስድስት ኪሎ፣ አራዳ፣ ተክሃይማኖት፣ መርካቶ፣ ለቡ፣ ቃሊቲ፣ ካሳንችስ፣ ቦሌ ሚሊኒየም፣ ወሎ ሰፈር፣ ጉርድ ሾላ፣ ገርጂ እና ለገሃር የክፍያ ማዕከላት) ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እና ቼክ ሊስት በማዘጋጀት እንዲሁም ለለሁሉ አገልግሎት ተብለው የገቡ ንብረቶች በአካል ምልከታ በማድረግ ነው፡፡

ክፍል ሁለት

ግኝቶች

የለሁሉ ኮንትራት አሠጣጥ ህግን የተከተለ፣ ውልን መሰረት ያደረገ እና የተሻለ አገልግሎት ለተጠቃሚው መስጠት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፤

የለሁሉ ኮንትራት በመንግስት እና በግል ሽርክና ግዥ ለመፈፀም በጥናት መሰረት መሆኑን በተመለከተ

25. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን በመንግስት እና በግል ሽርክና (Public Private partnership PPP) ግዥ ለመፈፀም ያስፈለገበትን አግባብ ማለትም (በመንግስት ሊሰጥ ስላለመቻሉ፣ በግል ቢሰጥ ስለሚያስገኘው ጥቅም ወዘተ) በጥናት መሰረት ሊወሰን ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታወቀው በመንግስት እና በግል ሽርክና ግዥ ለመፈፀም ያስፈለገበት ምክንያት በተመለከተ ጥናት ስለመከናወኑ እና የለሁሉ ኮንትራትን ለግል ሴክተር ለጨረታ ከማቅረቡ በፊት በመንግስት ተቋማት አገልግሎቱን መስጠት እንደማይቻል የተረጋገጠ ስለመሆኑ ማስረጃው ለኦዲት አልቀረበም፡፡

27. እንዲሁም ለግል ሴክተር ከመቅረቡ በፊት በመንግስት መ/ቤቶች ማለትም (እንደ ባንክ፣ ፖስታ ቤት ወዘተ) አገልግሎቱን መስጠት እንዲችሉ ባለመደረጉ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይቷል፡፡

- የመንግስት እና የግል ሽርክና በባህሪው በመንግስትና በግል ባለሀብቱ (ኮንሴሽነሩ) መካከል የሚደረግ ሽርክና በመሆኑ አገልግሎቱ በMonopoly በግል ሴክተሩ ብቻ እንዲያዝ ከማድረጉም በላይ የለሁሉ አገልግሎት (service based) በመሆኑ ሌሎች የክፍያ አማራጮች ለመጠቀምና አገልግሎቱ ማሳደግ ያልተቻለ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ ለለሁሉ ሴንተር ተብለው በተከፈቱ 34 ማእከሎች ብቻ መውሰኑ የተፈለገውን አገልግሎት ማቅረብ አልተቻለም፡፡ ነገር ግን ይህ አገልግሎት ለምሳሌ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚሰጥ ቢሆን በአዲስ አበባ በተለያዩ ቦታዎች ባሉ 422 ቅርንጫፎች፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት የሚሰጥባቸው 180 ቢሮዎች አገልግሎቱን በመስጠት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ከመሆንም አልፎ የአገር ሀብት (resource) በአንድነት ለተለያዩ አገልግሎቶች መጠቀም ያልተቻለ መሆኑ፤

- የለሁሉ አገልግሎት የሚሰጥባቸው የክፍያ ማእከላት ኪራይ በተገልጋይ ተቋማት (utilities) (የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ኢትዮ ቴሌኮም) ስለሚሸፈን ለተጨማሪ ወጪ እያስከተለባቸው መሆኑ፤
- ከ ብር 5000 በላይ የሚከፍሉ ደንበኞች ከባንክ ሲፒኦ አሰርተው የሚከፍሉበት አሰራር መኖሩ ይህም ደንበኞች የሲፒኦ ማሰሪያ ከብር 25 እስከ ብር 50 ተጨማሪ እንደሚከፍሉ ማድረጉ፤ በተጨማሪም በሲፒኦ የሚከፈል ክፍያ ተጣርቶ ገቢ ለማድረግ እስከ 15 ቀን እንደሚቆይ እና ይህም ገንዘቡ በውሉ መሰረት ለተገልጋይ ተቋማት (utilities) በ48 ሰአት ሳይገባ እንዲዘገይ ማድረጉ፤ ታውቋል፡፡

28. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሥራ ኃላፊዎች ይህን አይነት ሥራ ለመስራት የብሄራዊ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ባዘጋጀው ፕላት ፎርም በመጠቀም ክፍያዎችን በቀጥታ በተገልጋይ ተቋማት (utilities) ሂሳብ በማስገባት እና ለዚሁ አገልግሎት ሲባል ልዩ መስኮት በመክፈት እንዲሁም አገልግሎቱን ለመስጠት የሚፈልጉ የግል ባንኮች እና የግል ድርጅቶች (ኤጀንቶች) በማቀናጀት አገልግሎቱን በተቀላጠፈ እና ግልፅ በሆነ መንገድ ለመስጠት ዝግጅት አድርገው የነበረ ቢሆንም ከጨረታው መንግስት ከግሉ ዘርፍ የሚያደርገው ሽርክና PPP በመሆኑ የመንግስት ተቋማት መሳተፍ አይችሉም በሚል ውድቅ መደረጉን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ መረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ያዘጋጀውን ፕላት ፎርም ከኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ጋር እየሰሩበት እንደሆነ ጨምረው አስረድተዋል፡፡

29. ጉዳዩን አስመልክቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የተቀናጀ ክፍያ አገልግሎት የተጀመረበትን ሁኔታ የሚገልጽ እንጂ የለሁሉ ኮንትራት ለመንግስትና ለግል ሽርክና የተሰጠበትን ምክንያቶች አልገለጹም፡፡

30. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን በመንግስት እና በግል ሽርክና (Public Private partnership PPP) ግዥ ለመፈፀም ያስፈለገበትን አግባብ ጥናትን መሰረት ባለማድረጉ አገልግሎቱን ተደራሽ እንዳይሆን፣ በግል ተቋም በብቸኝነት እንዲቆጣጠር በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ አንድ አይነት እንዲሆን በማድረግ አገልግሎቱ እንዳያድግ እና እንዳይሻሻል አድርጓል፡፡

31. በተጨማሪም በመንግስት ተቋማት ይሁን በግል ሽርክና ቢሰጥ ስለሚያስወጣው ወጪ እና ሊገኝ ስለሚችለው ጥቅም (cost benefit analysis) ባለመሰራቱ የመንግስት ሀብት አሟጦ ለመጠቀም ያልተቻለ እና ለተጨማሪ የኪራይ ክፍያ ከመዳረጉም በላይ የለሁሉ አገልግሎት በመንግስት እና በግል ሽርክና ውል ተገቢ ነው ለማለት እንዳይቻል አድርጓል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ ክፍያ ሥርዓት ግዥ አፈፃፀምን በተመለከተ

32. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት በሀገሪቱ የሚኖረውን የተቀናጀ ክፍያ ስርዓትን የተመለከተ የአዋጭነት ጥናት ሊያደርግ እና ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) የፍላጎት መግለጫ (Need assessment) በመስራት ስምምነትን መሰረት ባደረገ መልኩ ሊሰራ ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታወቀው የለሁሉ ኮንትራት አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት በሀገሪቱ ሊኖር ስለሚችለው የተቀናጀ ክፍያ ስርዓትን የተመለከተ የአዋጭነት ጥናት ያላጠና መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም የአገልግሎቱ ባለቤት የሆኑት የተገልጋይ ተቋማት (utilities) የፍላጎት መግለጫ (Need assessment) አለመስራቱ የፍላጎት መግለጫ መሰራቱ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

34. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ቃለመጠይቅ ከቀረበላቸው ተገልጋይ ተቋማት (utilities) ማለትም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ኢትዮ ቴሌኮም እና የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን በሰጡት መልስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የፍላጎት መግለጫ እና የአዋጭነት ጥናት እንዳልተጠና እና እነሱም እንዳልተሳተፉ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም

የተለያዩ ተቋማት የቢሊንግ ሲስተም የተለያየ በመሆኑ በማቀናጀት ዩኒፋይድ ሲስተም በተገቢው ሁኔታ ያልተሰራ መሆኑን እንዲሁም ስራው ወደ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የወረደው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከግል ተቋሙ (ግሎባል ኮምፒውቲንግ ሶልሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር) ጋር ኮንትራቱን ተፈራርሞ መሆኑ ፍላጎታቸው አለመካተቱን ገልፀዋል፡፡

35. ጉዳዩን አስመልክቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና ከግል ድርጅቱ ጋር በመነጋገር ሥራዎችን ይሰሩ እንደነበር የገለፁ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውል ከመፈረሙ በፊት የተቀናጀ የክፍያ ሥርዓትን ስለመመስረት ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) ጋር የተሰራ ስራ ስለመኖሩ እና የፍላጎት መግለጫ ስለመሰራቱ ማስረጃው አልቀረበም፡፡

36. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት የተገልጋይ ተቋማት (utilities) (የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ የአዲስ አበባ ውሃ እና ፍሳሽ ባለስልጣን እና ኢትዮ ቴሌኮም) የተቀናጀ ክፍያ ስርዓትን የተመለከተ የአዋጭነት ጥናት ባለመጠናቱ እና የፍላጎት መግለጫ አለመሰራቱ በውሉ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጓል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ጋር ያደረገውን ውል በግዥ ሰነዱ መሰረት መሆኑን በተመለከተ

37. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግል/ማህበር ጋር ያደረገው ውል በግዥ ሰነዱ (Request for proposal (RFP)) መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

38. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች የሚከተሉት ተገኝቷል፡፡

- በኤክስፐረሽን ኦፍ ኢንተረስት ለተመረጡ ድርጅቶች በተላከው ሌተር ኦፍ ኢንቫይቴሽን RFP ላይ ይህ ኢንቫይቴሽን ለሌላ አካል አይተላለፍም ብሎ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን በኮንትራት ሰነዱ አንቀጽ 24 ላይ ውሉ ከሰብሲደሪ ወይም አሶሼት ካምፓኒ በስተቀር ለሶስተኛ ወገን መተላለፍ የማይቻል መሆኑ ተገልጿል፡፡ (…any assignment or transfer of USB contract or any rights hereunder by either party shall be prohibited except among the subsidiaries, Associates or Group companies of the partner)
  - በዚህም መሰረት ጨረታውን ያሸነፈው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር እ.አ.አ ሀምሌ 5 2011 ቁጥር UBS/0005/2011 በተጻፈ ደብዳቤ ኮንትራት አሳይመንት ለክፍያ ፋይናንሽያል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር ስራውን ያስተላለፈ እና ይህም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደ መሆኑ፣
  - ሌተር ኦፍ ኢንቫይቴሽን ላይ በተቀመጠው መሰረት ውል ያልተዘጋጀ እና ያልተፈረመ መሆኑ፤
  - ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር ከሰብሲደሪ ወይም አሶሼት ካምፓኒ አለመሆኑ፣
  - ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶልሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር ውስጥ ምንም አይነት ባለቤትነት ድርሻ እንደሌለው ከድርጅቶቹ መመስረቻ ጽሁፍ ለማወቅ ተችሏል፤
  - በተጨማሪም ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር የተቋቋመው የካቲት 2002 ዓ.ም ሲሆን የኮንትራት አሳይመንቱን ሲቀበል በጨረታው የሚጠይቀውን 5 ዓመት የስራ ልምድ እና ቢያንስ በ4 በመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ የሰራ የሚሉትን መስፈርቶች የማያሟላ ሆኖ ሳለ ኮንትራቱ ሙሉ በሙሉ ተላልፎ እንዲሰራ መደረጉ፤ ታውቋል፡፡

39. ጉዳዩን አስመልክቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በፍ/ብ/ ህግ ቁጥር 3201 እና 3202 መሰረት ውሉ እንዲተላለፍ ያደረጉ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም ስራውን ለመስራት ብቻውን ተወዳድሮ ማሸነፍ ለማይችል እና መስፈርቱን ለማያሟላ ድርጅት ተላልፎ መሰጠቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

40. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ጨረታ ካሸነፈው ድርጅት ጋር ያደረገው ውል በግዥ ሰነዱ (Request for proposal) መሰረት ባለመሆኑ የግዥ ሰነዱ

በተዋዋዩች መሰረት እንደ ህግ የሚያገለግል ስለሆነ ህግን ተላልፈዋል፡፡ እንዲሁም በውሉ እንደተቀመጠው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶልሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር ሰብሲደሪ ወይም አሶሼት ካምፓኒ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ መሰጠቱ ውልን መተላለፍ የሚያሳይ ከመሆኑ በላይ ጨረታው የሚጠይቀውን መስፈርት (qualifications) ለማያሟላ ድርጅት ተላልፎ በመሰጠቱ ተጠያቂነትን የማያጠናክር እና የተፈለገውን የአገልግሎት ጥራት ለደንበኞች ስለመሰጠቱ እንዳይረጋገጥ አድርጓል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ጋር ያደረገውን ውል ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ

41. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ከግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ያደረገው ውል በብሄራዊ ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

42. በአዲቱ ወቅት የተከለሰው የብሄራዊ ኢንፎርሜሽን እና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጂ እ/ኤ/አ ነሀሴ 2009 ላይ እንደተመለከተው የኢ-መንግስት አስተዳደር እና አገልግሎት ተግባራዊ የሚደረገው መንግስት ለመንግስት፣ መንግሰት ለንግዱ ዘርፍ፣ መንግስት ለዜጎች እና መንግስት ለሰራተኞች በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ ያተኮረ መሆኑ ተገልጾል፡፡ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ ክፍያ አገልግሎትን በተመለከተ ከግል ድርጅቱ ጋር ያደረገው ውል አባሪ 1 ገጽ 3 ላይ በአገልግሎቱ የተመረጡ የንግዱ ዘርፍ ለዜጎች የሚሰጠውን አገልግሎት ወደ ለሁሉ አገልግሎት መግባት እንደሚችሉ (ፖሊሲውን ባልተከተለ ሁኔታ) በውሉ ተገልፃል፡፡ ይህንኑ ተከትሎ ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማህበር (የግል ዘርፍ) ከአገር አቋራጭ አውቶብሶች ባለንብረቶች (ከሌላ የግል ዘርፍ) ጋር በመዋዋል የአገር አቋራጭ አውቶብሶች ትኬት በለሁሉ ማእከላት እየተሸጠ መሆኑ ከፖሊስው ውጭ ተግባራዊ መደረጉ ታውቋል፡፡

43. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የአገር አቋራጭ አውቶብስ ትኬት ሽያጭ የህዝብ አገልግሎት ተብለው ከተለዩት አንዱ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ለፓይለት ቴስት የተፈቀደ እና በቀጣይነት እንዲተገበር

ከትራንስፖርት ባለስልጣን ጥያቄ ቀርቧል ቢሉም ከፖሊሲው አንፃር ችግሩን የፈቱበትን ወይም ፓሊሲውን ስለማሻሻላቸው መልስ አልሰጡም፡፡

44. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፖሊሲው እንዳስቀመጠው በኢ. መንግስት ስትራቴጂ መሰረት ውል አለመፈጸሙ ፖሊሲው በትክክል እንዳይተገበር አድርጓል፡፡ እንዲሁም በአገልግሎቱ ተግባራዊ ለማድረግ ቢታመንበት እንኳ ፖሊሲው ማሻሻል ሲቻል ከፖሊሲው ውጭ ተግባራዊ መደረጉ ለሌላ ህገወጥ ሥራዎች በር ሊከፍት ይችላል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ጋር የዋጋ ድርድር ማድረጉን በተመለከተ

45. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት (unified billing system (UBS 1)) አሸናፊው ድርጅት ከግሎባል ኮምፒውቲንግ ሶልሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ጋር ዋጋ እና ከዋጋ ጋር ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች የሚያደርገው ድርድር በግዥ ህጉ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

46. ይሁን እንጂ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 45 ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ በተጠቀሰው መሰረት ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸም ግዥ ካልሆነ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ባቀረበው ዋጋ እና ከዋጋ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የመንግስት መ/ቤት ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ድርድር ማድረግ እንደማይቻል ተገልፆል፡፡ ነገር ግን አሸናፊው ተጫራች (ግሎባል ኮንፒቲን ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር) ለUBS 1 ያቀረበው ዋጋ ብር 1.43 ቢሆንም በኮንትራት ሰነዱ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከድርጅቱ ጋር ድርድር በማድረግ የተዋዋለው ዋጋ በብር 2.56 ቫትን ሳይጨምር መሆኑ፣ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

47. በተጨማሪም በውሉ መሰረት ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) በብር 1.13 እንዲጨምር በማድረግ በአጠቃላይ ከተቋማቱ የሚጠበቀው የደንበኛ ወርሃዊ የትራንዛክሽን ብዛት በአማካኝ 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺ) አካባቢ ሲሆን ለተገልጋይ ተቋማት (utilities) በወር ብር 1,017,000 (አንድ ሚሊዮን አስራ ሰባት ሺ ብር) ፣ በዓመት ደግሞ ብር 12,204,000 (አስራ ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ አራት ሺ ብር) ሲሆን ለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት ከየካቲት 2005 ዓ.ም እስከ ህዳር 2011 ዓ.ም ድረስ ማለትም የ5 ዓመት ከ 9 ወር ብር 70,173,000 (ሰባ ሚሊዮን አንድ ቶ ሰባ ሶስት ሺ ብር) ተጨማሪ የኮሚሽን ክፍያ አስከትሏል፡፡

48. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ "የዶላር ምንዛሬ መጠን 1.43 cost ሲሆን በዚህ ላይ በተመሰረተ (Per transaction price) PTP calculate ተደረገ እንጂ ዋጋ አልተሰጠም..." ብለዋል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ (Per transaction price) PTP calculate ለማድረግ የህግ አግባብ ስለመኖሩ፣ በየትኛው ገለልተኛ ባለሞያ (Independent expert) እንደተሰራ የሚገልፅ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም አንድ ተጫራች በዋጋ ማቅረቢያው (financeial proposal) ላይ የሚያስገባው አገልግሎቱን የሚሰጥበት ዋጋ እንጂ ለአገልግሎቱን ለመስጠት የሚያወጣው ዋጋ ባለመሆኑ የሰጡትን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

49. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት UBS 1 ባወጣው ጨረታ ላይ ከድርጅቱ ጋር የዋጋ ድርድር ማድረጉ ህግን ተከትለው እንዳያከናውኑ በማድረግ ተጠያቂነት እንዳይጠናከር አድርጓል፡፡ እንዲሁም የግዥ ህጉ ድርድር እንዲደረግ የሚፈቅዳቸው ግዥዎች ቢኖሩ እንኳን ዋጋ ለማስቀነስ ሆኖ እያለ በዚህ ውል ከቀረበው ዋጋ በላይ እንዲጨመር ድርድር መደረጉ የመንግስት እና የህዝብን ጥቅም እንዳይጠበቅ አድርጓል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታ ከማውጣቱ በፊት አማካኝ የደንበኛ ብዛት እና የጨረታ መነሻ ዋጋ ጥናት ማድረጉን በተመለከተ

50. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን ግገር ጨረታ ከማውጣቱ በፊት ተገልጋይ ተቋማት ያላቸውን የደንበኛ ብዛት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አማካኝ የደንበኛ ወይም ትራንዛክሽን ብዛት እና የጨረታ መነሻ ዋጋ ሊወስን ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደታየው ለ[(unified billing system (UBS 1 እና UBS 2)] ጨረታ ከመውጣቱ በፊት የጨረታ መነሻ ዋጋ (Estimated price) ሳይቀመጥ መከናወኑ እና በዚሁ ጨረታ ላይ ለፋይናንሻል ውድድር አንድ ተጫራች ብቻ ያለፈ ሲሆን ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ ጨረታውን እንዲያሸንፍ መደረጉ ታውቋል፡፡

52. እንዲሁም በጥናት ላይ የተመረከዘ አማካኝ የደንበኛ ብዛት አለመኖሩ፣ ነገር ግን በውሉ በተቀመጠው መሰረት ክትትል በማድረግ የአንድ ወር የተቀመጠው የደንበኛ ብዛት ለሁለት ተከታታይ ወራት 10% የሚጨምር ከሆነ (ማለትም የትራንዛክሽን ዋጋው የተሰጠው (ብር 2.56) በላይ በ10 በመቶ እንዲጨምር) ወይም የሚቀንስ ከሆነ

(ማለትም የትራንዛክሽን ዋጋው ከተሰጠው (ብር 2.56) በታች በ10 በመቶ እንዲቀንስ) የዋጋ ማስተካከያ እንደሚደረግበት ቢገልፅም ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

53. በተጨማሪም አማካኝ የደንበኛ ብዛት በተመለከተ የተለያዩ ጊዜ የተለያየ የደንበኛ ብዛት ስለ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

- የሶስቱን ተገልጋይ ተቋማት (utilities) አማካይ የደንበኛ ብዛት በግምት በወር 1,888,364 ትራንዛክሽን እንደሚኖር እና በዚህ ቁጥር ላይ በመነሳት በተከታታይ ሊኖር የሚችለውን ፕሮጀክሽን በማስላት ባቀረበው RFP ላይ ገልጾ ተጫራጮች የደንበኛ ብዛት በተመለከተ የራሳቸውን ጥናት እንዲያደርጉና በግምት በተቀመጠው ቁጥር ትክክለኛነት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊነት እንደማይወስድ የገለፁ መሆኑ፤
- በኮንትራት ሰነዱ ላይ አባሪ 8 Per transaction price የአንድ ወር ትራንዛክሽን 1,413,887 ቢሆን ለሁለት ተከታታይ ወራት 10% የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ከሆነ የዋጋ ማስተካከያ እንደሚደረግበት ቢገልፅም ይህ አሰራር ተግባራዊ አለማደረጉ፣
- በጃንዋሪ 2016 የተጠበቀውን የደንበኛ ብዛት ባለመገኘቱ እና ለሶስተኛ ግዜ አማካኝ የአንድ ወር ትራንዛክሽን ብዛት 950,000 ነው በማለት ውል እንዲሻሻል ቢያደርግም (amendment) የአንድ ወር ትራንዛክሽን ለሶስት ተከታታይ ወራት 10% የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ከሆነ የዋጋ ማስተካከያ እንደሚደረግበት ቢገልፅም ተግባራዊ አለመደረጉ፤

54. ጉዳዩን አስመልክቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ አማካኝ የትራንዛክሽን የመነሻ ዋጋ የተጠና ጥናት አለ ቢሉም ለኦዲት ቡድኑ በጥናት የተቀመጠ የመነሻ ዋጋ ማስረጃው ያልቀረበ እና በተደጋጋሚ እንዲቀርብ ቢጠየቅም አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም በወር ውስጥ ሊኖር የሚችለው አማካኝ የትራንዛክሽን ብዛት ባለመሟላቱ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት በውሉ መሰረት የሚጠበቀውን ገቢ ያላገኝ በመሆኑ እና በውሉ መሰረት ካሳ የጠየቀ በመሆኑ ውሉን በማራዘም ለማካካስ እንደቻሉ ገልፀዋል፡፡የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በግምት በተቀመጠ መረጃ ውል ማሰር ተገቢ ባለመሆኑ፣ እንዲሁም በወቅቱ በውሉ መሰረት ባለመተግበሩ የታቀደውን አላማ በጊዜ እና በውጤት እንዳይለካ በማድረጉ የሰጡት ምላሽ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

55. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለለሁሉ ኮንትራት ግዢ ጨረታ ከማውጣቱ በፊት ተገልጋይ ተቋማት (utilities) ያላቸውን የደንበኛ ብዛት ታሳቢ ያደረገ አማካኝ የትራንዛክሽን ዋጋ አለመወሰኑ የህግ አግባብ የተከተለ አሰራር እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ በተጫራቹ የቀረበ ዋጋ አነስተኛ መሆኑ ለመለየት እንዳይቻል ያደረገ መሆኑ፣ እንዲሁም ያለ ውድድር ባቀረበው ዋጋ እንዲያሸንፍና በመደራደር ከፍ ባለ ዋጋ ውል እንዲዋዋል ከማድረጉም በተጨማሪ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ ኢኮኖሚያዊ እና ፍትሃዊ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳይቻል እና የውሉ አላማ በጊዜ እና በውጤት እንዳይለካ አድርጓል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የአማካሪ ድርጅት ቅጥርን በተመለከተ

56. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት በተመለከተ አማካሪ ድርጅት ሲቀጥር በጨረታ ህጉ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

57. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥ ሰነድ (Request for proposal) እና ቢጋር (Terms of refefernce) በ Ji Yeon oh seoul korea በተባለ አማካሪ ድርጅት የተዘጋጀ ሲሆን አማካሪ ድርጅቱ በጨረታ ህጉ መሰረት ስለመቀጠሩ ለኦዲት ቡድኑ ማስረጃዎች አልቀረበም፡፡

58. እንዲሁም አማካሪ ድርጅቱን ለተቀናጀ ክፍያ አገልግሎት የግዥ ሰነድ Request for proposal ለማዘጋጀት የገባው ውል ስለመኖሩ፣ አማካሪ ድርጅቱ ይህንን የግዥ ሰነድ ለማዘጋጀት ያለው ችሎታ እና ልምድ ግምት ውስጥ ገብቶ ስራው ስለመሰጠቱ እና አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ የግዥ ሰነዱ(Request for proposal) ያዘጋጀ ስለመሆኑ እንዲሁም የተቀናጀ ክፍያ አገልግሎት በወቅቱ ለመስሪያ ቤቶችም ሆነ ለህገሪቱ አዲስ በመሆኑ አተገባበሩን በተመለከተ አስፈላጊውን ድጋፍ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለመስጠቱ ማስረጃዎች አልቀረቡም፡፡

59. ጉዳዩን አስመልክቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አማካሪ ድርጅት አልቀጠረም ሆኖም በኢክታድ ፕሮጀክት በወርልድ ባንክ በተቀጠረ አማካሪ Young consult የሚባል የኮሪያ ድርጅት ይማከር እንደነበር ገልፀዋል፡፡ የሥራ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በወርልድ ባንክ ተቀጠረ የተባለው አማካሪ ድርጅት ፕሮፋይል እና የተቀናጀ/ዩኒፋይድ/ ቢሊንግ ሥርዓት

የመዘርጋት የሚያስችል የተረጋገጠ ብቃት ያለው ስለመሆኑ እና ለመስራት በተዋዋለው አግባብ ተገቢውን የማማከር አገልግሎት ስለመስጠቱ መልስ አልሰጡም፡፡

60. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥን በተመለከተ አማካሪ ድርጅት ሲቀጥር በጨረታ ህጉ መሰረት ባለመሆኑ፣ ወይም በዕርዳታ/ድጋፍም ከሆነ ስራው የሚጠይቀውን አገልግሎት ለመስጠት በሚችል ድርጅት ስለመማከሩና በተቀጠረው መሰረት አገልግሎት ስለመስጠቱ ማረጋገጥ ካለመቻሉም በላይ ለሃገሪቱ አዲስ የሆነ የተቀናጀ/ዩኒፋይድ/ ቢሊንግ ስርዓት በተገቢው ጥልቀት ስለመጠናቱና ሌሎች አማራጮች ስለመታየታቸው እና ለሀገር እና ለዘርፉ ተመራጭ ስለመሆኑ ማረጋገጥ እንዳይቻል አድርጓል፡፡

በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ ወደ ለሁሉ አገልግሎት የሚገቡ አዲስ ተቋማትን በተመለከተ

61. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ ወደ ለሁሉ አገልግሎት የሚገቡ አዳዲስ ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ በጥናት መሰረት ስለመወሰኑ እና ተቋማቱ ለአገልግሎቱ የሚጠበቅባቸውን ዝግጅት ማድረጋቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

62. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው የለሁሉ አገልግሎትን ለመስጠት ከአሸነፈው ድርጅት (ግሎባል ኮምፒውቲንግ ሶልሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር) ጋር ውል የተገባው የአገልግሎት ዋጋ (ኮሚሽን) በትራንዛክሽን ብር 2.56 ነው፡፡ በዚሁ ውል ላይ ተጨማሪ አገልግሎት ወደ ለሁሉ ሲገባ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በመሆን የአገልግሎት ዋጋ (ኮሚሽን) እንደሚወሰን ተቀምጧል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢ.ቢ.ሲ) በሚያዝያ 2008 ዓ.ም የቴሌቪዥን ባለቤትነትና ባለይዞታነት ማረጋገጫ ክፍያ ለመሰብሰብ ከክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር የፋይናንሻል ሪካውንስሌሽን ፕሮሰስ ውል በመዋዋል ወደ ለሁሉ አገልግሎት የገባ ሲሆን ለአገልግሎቱ ለመክፈል የተስማማው በአንድ ትራንዛክሽን የአገልግሎት ዋጋ (ኮሚሽን) ብር 10.28 መሆኑ፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ የትራፊክ ማኔጅመንት በለሁሉ ማዕከላት በኩል ቅጣት እንዲሰበስብ ወደ ለሁሉ አገልግሎት እንዲገባ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደ ቢሆንም የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) በትራንዛክሽን 6.22 ብር የተወሰነ

መሆኑ፣ ይህም በጥናት ላይ ተመስርቶ የተወሰነ ስለመሆኑ እና የኮሚሽን ልዩነቱ ዝርዝር ምክንያት ማስረጃው አልቀረበም፡፡

63. እንዲሁም የለሁሉ አገልግሎት ውል መሰረት ያደረገው በወር በሚኖር አማካኝ የደንበኛ/የትራንዛክሽን ብዛት በመሆኑ ቀደም ሲል ከገባው ውል ተጨማሪ ደንበኛ የሚያገኝ ሲሆን ለአገልግሎቱ የሚያስፈልግ ቋሚ ወጪ (Fixed cost) የወጣ እና የተዘረጋ ጥላት ፎርም ያለው መሆኑ እና አዲስ በሚገቡ አገልግሎቶች በተከፈተው ማዕከል የሚስተናገዱ ሆኖ እያለ ከመጀመሪያው የውል ዋጋ ብር 2.56 በ 401% የበለጠ ዋጋ ኢ.ቢ.ሲ እና በ243% የበለጠ ዋጋ ለአ.አ ትራፊክ ማኔጅመንት የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍሉ መደረጉ ታውቋል፡፡

64. በተጨማሪም ኢ.ቢ.ሲ ወደ ውል ከመግባቱ በፊት ቢል ጀነሬት የሚያደርግበት እና ክፍያ የሚሰበስብበት እንዲሁም ደንበኞች ክፍያ ካልከፈሉ የሚቀጡበት የማቀናጀት ስርአት ሳይሰራ ወደ ለሁሉ አገልግሎት እንዲገቡ በመደረጉ በ2009 ዓ.ም ውል ማቋረጣቸው ታውቋል፡፡

65. ጉዳዩን አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው የኢ.ቢ.ሲ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ውሉ የተቋረጠው በትክክል የከፈለውን ደንበኛ ብዛት ማወቅ ስለማይቻል እና ሂሳቡ በትክክል ገቢ መደረጉን የሚያረጋግጥበት አሰራር ባለመኖሩ እና ገቢው በፊት ከሚሰበሰው አነስተኛ መሆኑን ምክንያት ውል ማቋረጣቸውን ገልፀዋል፡፡

66. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ኢ.ቢ.ሲ በራሱ በኩል መገንባት የሚገባውን ሲስተም ባለመገንባቱ እንዲሁም ኢ.ቢ.ሲ የሚፈልገው ማንኛውም ውሃ እና መብራት የሚከፍለውን ሰው በግዴታ የቴሌቪዥን ግብር ድርጅቱ እንዲያስከፍል ይጠይቅ ስለነበር እና ድርጅቱ ደግሞ ይህ ለማድረግ ስልጣን ስለሌለው ውሉ መቋረጡን ገልፀዋል፡፡እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ካሸናፊው ድርጅት ጋር ባደረገው የውል ሰነድ አንቀፅ 5 መሰረት አዲስ የሚገቡ ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ የሚወሰነው በግል ድርጅቱ እና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በመሆኑ በዚሁ መሰረት አዲስ ለገቡ ተቋማት የኮሚሽን ዋጋ መቀመጡን ቢገልፁም የኮሚሽን ዋጋው ከሌሎቹ አገልግሎት ክፍያ እንዲበልጥ እና የተለያየ ክፍያ የተወሰነው በጥናት ተደግፎ ስለመሆኑ መልስ አልተሰጠም፡፡

67. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ ወደ ለሁሉ አገልግሎት የሚገቡ አዲስ ተቋማት የኮሚሽን ክፍያ በጥናት መሰረት አለመወሰኑ ዘግይተው የሚገቡ ተቋማት በጥናት ላይ ባልተመሰረተ ሁኔታ የተጋነነ ክፍያ እንዲከፍሉ ከማድረጉም በላይ አዲስ በሚገቡ ተቋማት ምክንያት የሚያገኘውን ተጨማሪ ገቢ እና ቀደም ብሎ በተገቡት ውሎች የተሸፈኑ ቋሚ ወጪዎች (Fixed cost)፣ የተዘረጋ ፕላት ፎርም እና አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላትን ስለመገናዘባቸው ባለመታወቁ የተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና የህብረተሰቡን ፍላጎት ከግምት ስለመግባቱ ማረጋገጫ ካለመስጠቱም በላይ ሌሎች ተቋሞች የተቀናጀ/ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም እንዳይገቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

68. እንዲሁም ተቋማቱ ወደ ለሁሉ ውል ሲገቡ ከራሳቸው በኩል ማድረግ ስለሚገባቸው ዝግጅት፣ የሚዘረጋው ሲስተም ቼክ እና ባላንስ እንዲኖረው ሳይደረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የገቡ በመሆኑ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) እምነት እንዲያጡ ከማድረጉም በላይ የታሰበውን የተቀናጀ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዳይሆን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

የለሁሉ ኮንትራት አፈጻጸም የአገልግሎቱን በደንበኞች የስምምነት ሰነድ (service level aggrement) መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን መገምገም፤

በጨረታ ያሸነፈው ድርጅት ውል ላይ በተቀመጠው ቀን መሰረት አገልግሎት መስጠት መጀመሩን በተመለከተ

69. በጨረታ ያሸነፈው ድርጅት ውል ላይ በተቀመጠው ቀን አገልግሎት መስጠት ሊጀምር ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታወቀው UBS 1 ውል የተፈረመው እ.ኤ.አ ግንቦት 19/ 2011 ሲሆን በውሉ መሰረት ስራ የሚጀምርበት ቀን ሀምሌ 10 2011 እንደሆነ ቢገለጽም ስራ የጀመረው የካቲት 4 2013 ሲሆን ይህም የ18 ወራት ዘግይቶ መሆኑ፤

71. እንዲሁም UBS 2 ውል የተፈረመው እ.ኤ.አ ሰኔ 9 2014 (ሰኔ 2006 ዓ.ም) ሲሆን በውሉ ላይ ስራ የሚጀምርበት ቀን አለመገለጹ፤ ሆኖም ስራ የካቲት 2008 ዓ.ም የጀመረ መሆኑን፤

72. በተጨማሪም ለ UBS 2 (መቀሌ ፣ባህር ዳር ፣አዳማ እና ሃዋሳ ከተሞች) የአዳማ እና ሃዋሳ ከተሞች ስራ ያልተጀመረ መሆኑ እንዲሁም የባህር ዳር እና የመቀሌ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ወደ ተቀናጀ የክፍያ ስርዓት እስከ ኦዲቱ መጨረሻ አለመግባቱን ታውቋል፡፡

73. ጉዳዩን አስመልክቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ UBS 2 ከተመረጡ ክልሎች ጋር የሚሰራ በመሆኑ የክፍያ ሴንተሮቹ የሚያቀርበው መንግስት ስለሆነ በወቅቱ ቦታዎች መቼ ተዘጋጅተው ስራው መጀመር እንደሚቻል ስለማይታወቅ እንዲሁም ቦታዎች እንደተገኙ እና ስራው የሚጀመርበት ጊዜ መወሰን በወቅቱ ስላልተቻለ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሉን ከመዋዋሉ

በፊት ስራው እንዲከናወን የሚቻልበት ሁኔታ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) ጋር በመተባበር የውሉ ጊዜ እና ቦታ ሳይወሰን ውል ማሰሩ ተቀባይነት የለውም፡፡

74. በመሆኑም በጨረታውን ያሸነፈው ድርጅት ውል ላይ በተቀመጠው ቀን መሰረት ስራ አለመጀመሩ ስራው በውሉ መሰረት አጠናቆ ማስረከብ እንዳይችል አድጎታል፡፡ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሉን ሲዋዋል ስራ የሚጀመረበት ቀን ባለመገለፁ ስራው መቼ እንደሚጀመርና እንደሚያልቅ እንዳይታወቅ እና ስራው በእቅዱ መሰረት እንዳይከናወን አድርጎታል፡

አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት እና የአገልግሎት ተቋማቱ የፋይናንስ ሥርዓት አተገባበር በተመለከተ

75. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ያደረገው ውል መሰረት ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የሚሰበስቡትን የአገልግሎት ክፍያ በትክክል የሚያስተዳድሩ ስለመሆኑ አፈፃፀሙን ሊገመግም ይገባል፡፡

76. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆ ከታች የተዘረዘሩት የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት ከኢትዮ ቴሌኮም የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከለሁሉ የሚሰበሰበው ክፍያ ወደ መ/ቤታቸው በትክክል ገቢ እየተደረገ ነው ብለው ሙሉ በሙሉ መግለፅ እንደማያችሉ ቢሆንም አብዛኛው ጊዜ ገቢ እንደሚደረግ ነገር ግን በተሰበሰበው የቢል መረጃ ላይ በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈጠሩ ልዩነቶች የተነሳ እየተንከባለሉ ረጅም ወራት የቆዩ እንዳሉ ልዩነቶቹን ለማጥራት እና ትክክለኛ መረጃ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ስራ ከኢትዮ ቴሌኮም እና ከክፍያ ፋይናንሻል የተውጣጡ ባለሙያዎች እየሰሩ ቢሆንም ችግሩ እስካሁን እንዳልተቀረፈ ገልፀዋል፡፡
- እንዲሁም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጅ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከአዲስ አበባ ደንበኞች በ2005 ዓ/ም በመጋቢት እና በሚያዝያ ወር፣ በ2006 ዓ/ም ደግሞ ከጥቅምት እስከ መጋቢት ወር እንዲሁም በመቀሌ እና ባህርዳር

ሪጅን በየካቲት 2008 ዓ/ም ከተላለፈላቸው የቢል መጠን መካከል ደንበኞች ክፍያ ፈፅመዋል ተብሎ የተቀናነሰላቸው የገንዘብ መጠን በቢል ከወጣው ገንዘብ በብር 68,085.25 ያነሰ መሆኑንና ገንዘቡም ወደ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የባንክ ሂሳብ ገቢ ያልተደረገ መሆኑንና በድርጅቱና በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት መካከል የአሰራር ክፍተት እንዳለ በደብዳቤ ያሳወቁ ቢሆንም እስከ አሁን ምላሽ እንዳልተሰጣቸው ገልፀዋል፡፡

- የኦዲት ቡድኑ ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት የሰበሰበውን ገንዘብ በወር አንድ ጊዜ በባንክ ገቢ እንደሚያደርጉ ሲሆን፣ ነገር ግን በትክክል የከፈለውን ደንበኛ ብዛት ማወቅ ስለማይቻል ሂሳቡ በትክክል ገቢ መደረጉን ማረጋገጥ እንደማይቻል ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ውሉ ከተቋረጠ በኋላ ለ4 ወር ያህል ያለ ኮሚሽን ክፍያ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት የቴሌቪዥን ባለቤትነትና ባለይዞታነት ክፍያ ሰብስቦ ወደ ባንክ ሂሳባቸው ማስገባቱን እና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት ያለ አገልግሎት ክፍያ (ያለ ኮሚሽን) ለመስራት ጥያቄ ማቅረቡን ገልፀዋል፡፡

77. በተጨማሪም ተገልጋይ ተቋሚት ለሰጡት አገልግሎት የሰበሰቡት ክፍያ ዝቅተኛ መሆኑ እና የክፍያ ስርዓቱ ውጤታማ አለመሆኑ ለማሳያ ያህል፡-

- የአዲስ አበባ ውሃ ፍሳሽ ባለስልጣን ለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት የካቲት ከ2005 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 2010 ዓ.ም (ከ6 ዓመት በላይ) እንዲሰበሰብለት የላከው ዳታ የገንዘብ መጠን ብር 6,472, 048,746.9 (ስድስት ቢሊዮን አራት መቶ ሰባ ሁለት ሚሊዮን አርባ ስምንት ሺ ሰባት መቶ አርባ ስድስት ብር ከ6/100) ሲሆን የተሰበሰበው ብር 3,198,033,890.00 (ሶስት ቢሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ስምንት ሚሊዮን ሰላሳ ሶስት ሺ ስምንት መቶ ዘጠና ብር) 49.4% መሆኑን፤
- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በአዲስ አበባ በለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት ከጥር 2005 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2010 ዓ.ም (ከ6 ዓመት በላይ) እንዲሰበሰብለት የላከው ዳታ የገንዘብ መጠን ብር 6,318,693,418.68 (ስድስት ቢሊዮን ሶስት መቶ አስራ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና ሶስት ሺ አራት መቶ አስራ ስምንት ብር ከ68/100) ሲሆን የተሰበሰበው ብር 3,879,997,662.74 (ሶስት ቢሊዮን ስምንት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ስድስት መቶ ስልሳ ሁለት ብር ከ74/100) 61% መሆኑን፤

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በመቀሌ እና በባህርዳር ለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት ከየካቲት 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2010 ዓ.ም (2 አመት ከ4 ወር) እንዲሰበሰብለት የላከው ዳታ የገንዘብ መጠን ብር 488,227,105.02 (አራት መቶ ሰማንያ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አንድ መቶ አምስት ብር ከ02/100) ሲሆን የተሰበሰበው ብር 246,537,910.52 (ሁለት መቶ አርባ ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አስር ብር ከ52/100) 50.4% መሆኑን
- ኢትዮ ቴሌኮም በአዲስ አበባ ለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት ጥር ከ2005 ዓ.ም እስከ መጋቢት 2010 ዓ.ም እና በመቀሌ እና ባህር ዳር በለሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት ከየካቲት 2008 ዓ.ም እስከ መጋቢት 2010 ዓ.ም እንዲሰበሰብለት የላከው ዳታ የገንዘብ መጠን 7,528,986,345 ሲሆን የተሰበሰበው 5,374,549,850.9 (71%) መሆኑን ታውቋል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡በለሁሉ ኮንትራት ሊሰበሰብ የታቀደ እና የተሰበሰበ ገንዘብ ልዩነት

የተቋሙ ሥም	ዓመት	ሊሰበሰብ የታቀደ በብር	የተሰበሰበ በብር	አፈጻጸም በመቶኛ
የአዲስ አበባ ውሃ ፍሳሽ ባለስልጣን	5 ዓመት ከ5 ወር	6,472, 048,746.9	3,198,033,890.00	49.4%
የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ አገልግሎት አዲስ አበባ	5 ዓመት ከ3 ወር	6,318,693,418.68	3,879,997,662.74	61%
የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ አገልግሎት በመቀሌ እና ባህር ዳር	2 ዓመት ከ4 ወር	488,227,105.02	246,537,910.52	50.4%
የኢትዮ ቴሌኮም	የአዲስ	7,528,986,345	5,374,549,850.9	71% *

በአዲስ አበባ፣መቀሌ እና ባህር ዳር	አበባ 5 ዓመት ከ1ወር እና የመቀሌ እና ባህር ዳር 2 ዓመት ከ 1 ወር			

78. ከላይ በሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው ተገልጋይ ተቋማት (utilities) ለሰጡት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ክፍያቸውን መሰብሰብ ቢኖርባቸውም የአዲስ አበባ ውሃ ፍሳሽ ባለስልጣን ብር 3,274,014,857 (ሶስት ቢሊዮን ሁለት መቶ ሰባ አራት ሚሊዮን አስራ አራት ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ ሰባት ብር) 50.6% ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ አገልግሎት አዲስ አበባ ብር 2,438,695,756 (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሰባት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር) 39% ያልተሰበሰበ መሆኑ እና የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ አገልግሎት በመቀሌ እና ባህርዳር ብር 241,689,194 (ሁለት መቶ አርባ አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ዘጠና አራት ብር) 49.6% ያልተሰበሰበ በመሆኑ እንዲሁም የኢትዮ ቴሌኮም በአዲስ አበባ፣ በመቀሌ እና በባህር ዳር 2,154,436,494 ብር ይህም ሊሰበሰብ ከሚገባው 29% ያልተሰበሰበ መሆኑ ነገር ግን ከኢትዮ ቴሌኮም ወደ ለሁሉ ማዕከላት የሚላከው ዳታ ለቴሌ ሾፕ ስለሚላክ የኢትዮ ቴሌኮም ደንበኞች በቴሌ ሾፕ ሊከፍሉ ስለሚችሉ አፈጻጸሙን ለመደምደም አያስችልም፡፡ ተገልጋይ ተቋማቱ በለሁሉ የክፍያ ስርአት የአገልግሎት ክፍያቸው ሙሉ በሙሉ ተሰብስቦ ገቢ እየተደረገ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተገልጋይ ተቋማት (utilities) የገንዘብ አሰባሰብን በተመለከተ ያለበት ሁኔታ ክትትል በማድረግ የተጠቀሰውን ያህል ገንዘብ ያልተሰበሰበበትን ምክንያት እንዲጣራ በማድረግ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ አለመደረጉ እና ለልዩነቶቹም መፍትሄዎች አለመቀመጣቸው ችግሮቹ ሳይለዩ እንዲቆዩ አድርጓል፡፡

79. ስለ ጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ በፋይናንስ ሪኮንስሌሽን ውል መሰረት በተቋማቱ እና በክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መሀከል ተግባራዊ የሚደረግ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

80. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ አፈፃፀሙን ባለመገምገሙ እና ክትትል ባለማድረጉ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) ለሰጡት አገልግሎት መሰብሰብ ያለባቸውን የገንዘብ መጠን እንዳይሰበስቡ በማድረግ የመንግስት ገቢ በትክክል እና በግልጽ የሚሰበሰብበት ስርአት እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ ተጠያቂነትን እንዳይጠናከር አድርጓል፡፡

በተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) አስተዳደርን በተመለከተ

81. በተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና በግል ድርጅቱ መሃከል የሚደረግ የአገልግሎት ክፍያ ውልን መሰረት ያደረገ ግልፅ እና ተጠያቂነትን በተላበሰ መልኩ ሊፈፀም ይገባል፡፡

82. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት ኮሚሽን አወሳሰድ በውሉ መሰረት ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ ከታች የተዘረዘሩት የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

83. አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) ጋር ባደረገው የfinancial reconcilation process ውል መሰረት በየጊዜው ከሚሰበስበው የተቋማቱ ገቢ ላይ የራሱን ድርሻ ኮሚሽን (አድቫንስ) የሚወስድ እና ቀሪውን ወደ ተቋማቱ የባንክ ሂሳብ የሚያስገባ መሆኑ ተገልፃል፡፡ ሆኖም ክፍያ ፋይናንሻል በውሉ መሰረት አድቫንስ መቀነሱን /መውሰዱን/ ለተገልጋይ ተቋማት (utilities) በማሳወቅ ሂሳባቸውን በየወሩ ቼክ እና ባላንስ በመስራት እንደማይረጋገጥ ታውቋል፡፡

84. በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ ለተገልጋይ ተቋማት (utilities) ከተገኘው ማስረጃ እና ከቀረበ ቃለ መጠይቅ እንደታየው ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር የኮሚሽን ክፍያ እንዲሰጠው እንደሚጠይቅ እና በጥያቄው መሰረት እንደሚከፈለው ታውቋል፡፡ (ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ወደ ክፍያ አካውንት ትራንስፈር

እንደሚደረግ፣ ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ የትራፊክ ቅጣት እና ከቴሌ በቼክ እንደተቀበለ) ማስረጃዎች ቀርበዋል፡፡

85. ጉዳዩን አስመልክቶ ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለመጠይቅ በሰጡት ምላሽ በውሉ መሰረት አድቫንስ የሚቀንሱ ሲሆን ነገር ግን ለተገልጋይ ተቋማት (utilities) ኮሚሽን ያልተቀነሰበት ሂሳብ በማስገባት እና ኮሚሽን በመጠየቅ የተቀነሰውን ሂሳብ እንዲካካስ የሚያደርግበት አሰራር እንዳለ አስረድቷል፡፡ ሆኖም የቀነሰው የኮሚሽን ሂሳብ እንዲካካስ ወጥ በሆነ መልኩ የሚጠይቅበት እና የሚቀበልበት ሁኔታ አለመኖሩን ተመልክተናል፡፡ ለማሳያ ያህል ውል ከተጀመረበት መጋቢት 2013 እስከ ነሃሴ 2018 በ6 ዓመት ውስጥ ከኢትዮ ቴሌ ኮም የተከፈለው ኮሚሽን ማርች 14 እስከ ጃንዋሪ 2015 የ11 ወር ብቻ መሆኑ፣የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከየካቲት 2018 እስከ ነሐሴ 2018 የ7 ወር ኮሚሽን ክፍያ ያልተጠየቀ እና ያልተከፈለው መሆኑ፣ የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ሰኔ 2017 እስከ ነሐሴ 2018 የ15 ወር ኮሚሽን ክፍያ ያልተጠየቀና ያልከፈለው መሆኑ፤ እንዲሁም የአዲስ አበባ ውሃ እና ፍሳሽ ባለስልጣን ከመስከረም 2017 እስከ ነሐሴ 2018 የ12 ወር ኮሚሽን ክፍያ ያልከፈለ በመሆኑ የሚካካሰው ክፍያ ምንጭ ከየት የመጣ መሆኑን ማስረዳት አልቻሉም፡፡ በመሆኑም የኮሚሽን ክፍያ ግልፅ፣ ተጠያቂነትን የሚያሳይ እና በየጊዜው የሚታረቅ የገቢ ሂሳብ አያያዝና አስተዳደር አለመኖሩ ታውቋል፡፡

86. በመሆኑም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አገልግሎት የሚሰጠው የግል ድርጅት የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) አወሳሰድ በውሉ መስረት ስለመሆኑ ክትትል ባለመደረጉ የግል ተቋሙ ከውሉ ወጪ ለአሰራር በሚያመቸው መንገድ የኮሚሽን ክፍያ የሚወስድበት ሁኔታ በመፍጠር አሰራሩ ለተገልጋይ ተቋማትም (utilities) ሆነ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ግልጽ አለመሆኑ ለሌላ ህገወጥ ሥራዎች በር ሊከፍት ይችላል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ሥርዓቱን ለመከታተል የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

87. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ከግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ባደረገው ውል መሰረት የፋይናንስና የክፍያ ሥርዓቱን የሚከታተልበት ስርአት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

88. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች የሚከተሉት ታይተዋል፡፡

89. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በUBS 1&2 ውል አባሪ 8 ገጽ 2 መሰረት፡-

- ሴኪዩሪቲ ዲፖዚት (security Deposit) እንደ ማስተማማኛ እንዲቀመጥ ይህም በየጊዜው ዝቅተኛ ባላንስ መጠኑ እንዳይጎድል ማሻሻያ የሚደረግበት ለእያንዳንዱ UBS 1&2 ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ) እንዲሆን እንዲሁም ቅጣቶች በሚኖርበት ጊዜ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየወሩ ከተቀመጠው ገንዘብ እንደሚቀንስ የተገለፀ ቢሆንም በውሉ መሰረት ተግባራዊ አለመሆኑ፤
- ለUBS 1 የስራ ማስፈፀሚያ ዋስትና (Performance guarantee in opretion period) ብር 1,800,000 ከግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ኮንትራቱን እስኪጨርስ ድረስ ክትትል እየተደረገ መታደስ እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም ጨረታ ካሸነፈ ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ እንዲያስቀምጥ አለመደረጉ፤
- ለUBS 2 የስራ ማስፈፀሚያ ዋስትና (Performance guarantee in opretion period) ብር 2,200,000 ከግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ኮንትራቱን እስኪጨርስ ድረስ ክትትል እየተደረገ መታደስ እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም ጨረታ ካሸነፈ ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ እንዲያስቀምጥ አለመደረጉ፤ ታውቋል፡፡

90. በኦዲቱ ወቅት ለኢትዮ ቴሌኮም የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በቀረበ ቃለመጠይቅ በሰጡት ምላሽ ከክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተለያዩ ክፍያዎች በመሰብሰብ ዳታው በ24 ሰዓት ጥሬ ገንዘቡ በ48 ሰዓት ወደ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) ገቢ ማድረግ ቢኖርበትም ክፍያው እስከ 5ቀን ገቢ ሳይደርግ የሚያቆይ መሆኑን፤ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ኢትዮ ቴሌኮም በሁሉ ማዕከላት የአገልግሎት ክፍያው እንዲሰበሰብ ከጀመሩ ከ2005 ዓ.ም እስካሁን የ11 ወራት ብቻ የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) ለግል ተቋሙ የከፈሉ ሲሆን እስከ Nov.2018 መክፍል የነበረባቸው አጠቃላይ የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) ብር 41,091,690.30 ሲሆን ነገር ግን የዳታ እና የገንዘብ በውል በተቀመጠው ጊዜ መሰረት ባለማስተላለፋቸው እና በመዘግየታቸው ምክንያት ብር 47,473,662.09 እንደቀጧቸው ይህም አገልግሎት ከሰጡት (ሊከፈላቸው ከሚገባ የኮሚሽን ክፍያ) በበለጠ መጠን ብር 6,381,971.70 እንደተቀጡ ገልፀዋል፡፡

91. ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ድርጅታችን ከኢትዮ ቴሌኮም በገባው ውል መሰረት በ24 ሰዓት ውስጥ የተሰበሰበውን ዳታ በተጨማሪም በ48 ሰዓት ውስጥ የተሰበሰበውን ገንዘብ ገቢ ስለሚያደርግ የተቆረጠብን ኮሚሽን የለም፤ ያለ ኮሚሽን ሊሰሩ እንደማይችሉ ገልፀዋል፡፡

92. እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ተገልጋይ ተቋማት (utilities) በግል ድርጅቱ ሊከፈል የተዘጋጀ እና የተከፈለ የክፍያ መጠን የሚከታተሉበት ሲስተም (Dash Board view) ስለመኖሩ ማስረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ጊዜ ድረስ አልቀረበም፤

93. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በውሉ መሰረት ሴኪውሪቲ ዲፖዚት እና የስራ ማስፈፀሚያ ዋስትና(Performance guarantee in opretion period) ስለመኖሩ ክትትል እንዳላደረጉ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም (Dash Board view) በተመለከተ ስራው እንደተጀመረ የተዘጋጀ እና በኢ-መንግስት ዳይሬክቶሬት በኮምፒተር ይታይ እንደነበረ ሆኖም በተደጋጋሚ የመብራትና የኔትወርክ መቆራረጥ ችግር ምክንያት በአገልግሎት አቅራቢው በኩል የሚመጡ ደንበኞች ኦፍ ላይን ማስተናገድ የሚችል በመሆኑ ሲስተሙ ትክክለኛውን መረጃ ሊያሳይ ባለመቻሉ እንዲቋረጥ መደረጉን ገልፀዋል፡፡

94. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ባደረገው ውል መሰረት የፋይናንስና የክፍያ ሥርዓቱን የሚከታተልበት ስርአት ባለመዘርጋቱ በውሉ መሰረት ባለመተግበሩ መቀጣት ያለበትን ገንዘብ እንዳይቀጣ በማድረግ፣ የክፍያ ስርዓቱ የተወሳሰበ እና ግልፅ እንዳይሆን አድርገዋል፡፡ እንዲሁም የግል ደርጅቱ በውሉ መሰረት ዳታ እና ጥሬ ገንዘብ ገቢ ካላደረገ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) በምን ዓይነት መልኩ መቅጣት እንዳለባቸው ግንዛቢ እንዳይኖራቸው እና ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖር አድርጓል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅትን

የፋይናንስ ኦዲት ማድረጉን በተመለከተ

95.የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት የሚያከናውነው የግል ድርጅት የሂሳብ ኦዲት ሪፖርት በማስደረግ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በየአመቱ የሚያቀርብበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

96.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት በገለልተኛ አካል ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሪፖርቱን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይልክ መሆኑ ታውቋል፡፡

97. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ለክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጅ ኃ/የተ/የግ/ማ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ድርጅታቸው ከለሁሉ አገልግሎት በተጨማሪ ሌሎች ስራዎች እንደሚሰራ እና እንደ ድርጅት ኦዲት እንደሚያስደርግ፣ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያሳውቅበት አሰራር አለመኖሩ ገልፀዋል፡፡

98.ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት ኦዲት የሚያስደርግ ሲሆን ሪፖርቱን የማይልክ መሆኑ እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል በውጪ ኦዲተር ለማሰራት በጀት ተይዞ ተግባራዊ አለመደረጉን ገልፀዋል፡፡

99.በመሆኑም የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት የሚያከናውነው የግል ድርጅት የሂሳብ ኦዲት ሪፖርት በማስደረግ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በየአመቱ የሚያቀርብበት ስርዓት ባለመዘርጋቱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኦዲት ሪፖርት መሰረት ክትትል በማድረግ ችግሮችን ለመፍታት እንዳይቻል አድርጓል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎት የሚሰጡ

ማዕከላትን ማቅረቡን በተመለከተ

100. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ሰነድ አንቀጽ 5 መሰረት 41 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በአዲስ አበባ እንዲሁም 14 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በክልል ከተሞች እንዲከፈቱ በማድረግ አገልግሎቱን በተቀላጠፈ መንገድ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይገባል፡፡

101. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረበ ቃለ መጠይቅ እንደታየው ለአዲስ አበባ በUBS 1 ውል 34 የክፍያ ማዕከላት ብቻ መከፈታቸውን በውሉ ውስጥ የተካተተው 7 ማዕከላትን በመክፈት አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ፤

102. እንዲሁም UBS 2 መከፈት ከነበረበት 14 ማዕከላት ውስጥ መቀሌ እና ባህርዳር በ8 ማዕከላት ብቻ የተከፈተ ሲሆን በዚሁ ማዕከል አገልግሎት እየተሰጠ ያለው የመብራት እና የስልክ አገልግሎት ብቻ መሆኑ፤ እና እስከ አሁን ድረስ የውሃ ክፍያ አገልግሎት በማዕከላቱ መክፈል ያልተጀመረ መሆኑ፣ እንዲሁም አዳማና ሃዋሳ ምንም አይነት ስራ እንዳልተጀመረ እና አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በውሉ መሰረት አለመከፈታቸው ታውቋል፡፡

103. በተጨማሪም ለኦዲቱ በናሙና ከተመረጡ 17 የክፍያ ማዕከላት ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በ12ቱ ማዕከላት አገልግሎት እየሰጡ ያሉትን የክፍያ ማዕከላት ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዳልሆኑ በየአቅራቢያው ሌሎች ተጨማሪ ማእከላት መከፈት እንዳለባቸው ገልፀዋል፤ በተጨማሪም በአየር ጤና ማዕከል ከኦሮሚያ ክልል እና በጉርድ ሾላ የክፍያ ማዕከል ከቦሌ አራብሳ ድረስ በመምጣት የሚከፍሉ ደንበኞች እንዳሉ ገልፀዋል፡፡

104. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ ማዕከላት ውስጥ አገልግሎት ለማግኘት ለመጡ ለ170 ደንበኞች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለክፍያ ከተለያየ አካባቢ መጥተው ረዥም ሰዓት የሚሰለፉ መሆኑ፣ አገልግሎቱ በተሻለ ማግኘት አለመቻሉን ለምሳሌ ከባንክ አካውንት ተቆራጭ የሚደረግበት ስርዓት ቢዘረጋ የተሻለ አገልግሎት መስጠት ይቻል እንደነበር ገልፀዋል፡፡

105. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ቅድመ ዝግጅት ስለሚያስፈልግ እና አገልግሎት የሚሰጥባቸው የክፍያ ማእከላት የማቅረብ ግዴታ የመንግስት ስለነበር ማእከላቱን ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ለማግኘት ጊዜ በመውሰዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

106. በመሆኑም በቂ የሆኑ የክፍያ ማዕከላት ባለመከፈታቸው ደንበኞች ተሰልፈው መክፍላቸው እና መስተጓጎላቸው እንዲሁም ውል ላይ የተካተቱ አገልግሎቶች በለሁሉ የክፍያ

ማዕከላት አለመክፈላቸው በተጨማሪም አገልግሎቱን በተቀላጠፈ መንገድ እንዳይሰጥ እና ህብረተሰቡ አገልግሎቱን በወረፋ እንዲያገኝ አድርጓል፡፡

የለሁሉ አገልግሎት መስጫ የቀረቡ ቢሮዎችን በተመለከተ

107. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ አገልግሎት መስጫ ያቀረባቸው ቢሮዎች በቂ እና ምቹ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ስለመሆናቸው ሊከታተል ይገባል፡፡

108. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በውሉ መሰረት አገልግሎት መስጫ ቢሮ ማቅረብ ቢኖርበትም ይህ ጉዳይ ወደ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የተሸጋገረ በመሆኑ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) ያላቸው ቢሮዎች በመስጠትና ሌላ ተጨማሪ ቢሮዎች በመከራያት በማቅረባቸው በዚህ ውል መሰረት ከሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) በተጨማሪ ለኪራይ ወጪ መዳረጋቸውን ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ከኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን ከኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ቤቴል አካባቢ ስፋቱ 194.55ካሬ ሜትር በካሬ ብር 200 በወር ብር 38,910 ለመክፈል በቀን 21/9/2004 ዓ.ም የኪራይ ውል የፈፀመ ሲሆን ከግንቦት 1 2005 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 2011 ዓ.ም ብር 2,568,060 የኪራይ ክፍያ ዕዳ ያለበት መሆኑ፣
- ኢትዮ ቴሌኮም ከኢትዮጵያ መድህን ድርጅት ከመጋቢት 6 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የተከራየ ቢሆንም የቢሮ ኪራይ እንዲከፍሉ እና ውላቸው እንዲያድሱ በተደጋጋሚ ቢጠየቁም ያልተከፈለ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ የየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የለሁሉ አገልግሎት የሚሰጥበትን ቢሮ ክፍለ ከተማው በደብዳቤ በቁጥር የካ/ስ1/1264/11 በቁጥር 8/01/11 ቢሮ እንዲለቁ የጠየቁ መሆኑ፤
- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ያቀረበው በመገናኛ በሚገኘው ዋና መስሪያ ቤት ግቢ ውስጥ እና የመካኒሳ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ውስጥ ከ6 አመታት በላይ እየተገለገሉበት ሲሆን ነገር ግን ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የቢሮ እጥረት ስላጋጠመው ሁለቱንም ቢሮዎች በተከታታይ ባሉት 60 ቀናት እንዲለቅለት በደብዳቤ የገለፁ መሆኑ ታውቋል፡፡

109. እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቁጥር 001-1/በዝ/2907/09 በቀን 12/04/09 በተጻፈ ደብዳቤ የአራት ኪሎ የለሁሉ ክፍያ ማእከል ቢሮ የህንጻ እድሳት የሚፈልግ፣ የደንበኞችንና የማዕከሉን ሰራተኞች ጤና የሚጎዳ የመጸዳጃ ቤት ችግር ያለበትና የማዕከሉን አርማ በህንጻው ላይ ለማስቀመጥ ህንጻውን ያከራየው ቤተ ክህነት የተከለከለ መሆኑ ለህብረተሰቡ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ የተገለፀ መሆኑ፤

110. በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ ለግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ባቀረበው ጥያቄ የክፍያ ማእከሉ ቢሮዎች የኢትዮ ቴሌ እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሲሆኑ ኪራዩን የሚከፍሉት እነኚሁ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) መሆናቸውን ገልፀው፤ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት ቢሮ በራሱ ለማቅረብ ጠይቀው እንዳልተፈቀደ ገልጸዋል፡፡

111. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለሁሉ ኮንትራት ውል መሰረት ቢሮ ማቅረብ ቢኖርበትም ተገልጋይ ተቋማት (utilities) እንዲያቀርቡ ማድረጉ ለተገልጋይ ተቋማት (utilities) ተጨማሪ ወጪ ከማስከተሉ በተጨማሪ በተቋማቱ እና ከሌሎች ድርጅቶች የተከራዮዋቸውን ቢሮዎች እንዲለቁ በየጊዜው መጠየቃቸው እና ኪራይ ባለመክፈላቸው የተያዙት ቢሮዎች ቀጣይነት አስተማማኝ አለመሆኑ አገልግሎቱ በተቀላጠፈ መንገድ እንዳይሰጥ አድርጓል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቀረጥ ነፃ የገቡ ንብረቶች አያያዝን በተመለከተ

112. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ውል መሰረት ከቀረጥ ነጻ የገቡ ንብረቶችን ዋስትና መድህን (Insurance) መግባታቸውን፣ የውል ጊዜው ሲጠናቀቅ ለመረከብ በሚያመች መልኩ ስለመያዛቸው ሊከታተል እና በየአመቱ ቆጠራ ሊያደርግ ይገባል፡፡

113. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው ለለሁሉ አገልግሎት የገቡት ንብረቶች የመድህን ኢንሹራንስ ያልተገባላቸው መሆኑ፤

114. እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ግሎባል ኮምፒውቲንግ ሶልሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ባደረገው ውል መሰረት ለUBS 1 41 እንዲሁም ለUBS 2 14 የለሁሉ ክፍያ ማእከላት የሚያስፈልጉ እቃዎች ገዝቶና አደራጅቶ ስራውን እንዲሰራ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፍቃድ አግኝተው ከቀረጥ ነጻ የገቡ እቃዎች ያሉ ሲሆን የእቃዎቹ ዝርዝር መረጃ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኝ አለመሆኑ፣ ለእያንዳንዱ ጣቢያ ምን ያህል እቃ እንደገባ እና አሁን በስራ ላይ ያለው ተለይቶና ተረጋግጦ የማያውቅ በመሆኑ እንዲሁም የውሉ ጊዜው ከማለቁ በፊት ዝርዝር ተወስዶ ቁጥጥር ለማድረግ በሚያመች መልኩ ቁጥር ተሰጥቶና ተመዝግቦ አለመያዙ፤

115. በተጨማሪም በፌደራል መንግስት ግዢ አፈጻጸም ማንዋል ሀምሌ 2002 መሰረት በፋይናንስ ህጎች መሰረት በየጊዜውና በየዓመቱ ንብረት ቆጠራ መደረግ እንዳለበት ቢገልፅም የለሁሉ አገልግሎት ስራ ከጀመረበት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በየአመቱ የንብረት ቆጠራ አለመደረጉ፣ እንዲሁም በ2010 ዓ.ም በለሁሉ ማዕከላት የንብረት የቆጠራ መረጃ ለኦዲት ቡድኑ ቢቀርብም የተሞላ አለመሆኑ፣ ከገባው ንብረት አንፃር በንፅፅር አለመቀመጡ፤ ታውቋል፡፡

116. ጉዳዩን አስመልክቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ኮንትራቱ በሚያበቃበት ወቅት ለርክክብ በሚያመች መልኩ ቆጠራ ተደርጎ ተይዟል ነገር ግን በየዓመቱ ቆጠራ አላደረግንም ቢሉም መጀመሪያ ከገባው ንብረት ጋር ተገናዝቦ የተያዘበት ማስረጃ ባለመቅረቡ ንብረት ላይ ተገቢ ቁጥጥር ተደርጓል ለማለት አይቻልም፡፡

117. በመሆኑም ለለሁሉ አገልግሎት ተብለው የገቡ ንብረቶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተመዝርበው ባለመያዛቸው ቁጥጥሩ የላላ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ እንዲሁም የለሁሉ ኮንትራት ውል መሰረት ከቀረጥ ነጻ የገቡ ንብረቶች በየአመቱ ቆጠራ ባለመደረጉ የንብረቶቹ አጠቃላይ ሁኔታ እንዳይታወቁ ከማድረጉ በላይ ንብረቶቹ ለታቀደላቸው አላማ ብቻ ስለመዋላቸው ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም ንብረቶቹ የመድህን ዋስትና ያልተገባላቸው መሆኑ ለንብረቶቹ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ እንዳልተደረገለት ማሳያ ነው፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት

ሲስተም ኦዲት ማስደረጉን በተመለከተ

118. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት ሲስተም ሶፍትዌር ኦዲት (system audit) በማካሄድ ከሲስተሙ የሚወጣው ሪፖርት ትክክለኛነት ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

119. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠየቆች እንደታየው ጨረታውን ካሸነፈው የግል ድርጅት ጋር ባደረገው ውል አባሪ 2 ገጽ 2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወጪውን በመሸፈን በሶስተኛ ወገን ቢያንስ በአመት ሁለት ጊዜ ሲስተም ኦዲት ማስደረግ እና ጥራቱን ማረጋገጥ እንዳለበት ቢገለጽም ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

120. እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና ከለሁሉ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ባደረገው ምልከታ እና ከዶክመንት ማስረጃዎች የለሁሉ አገልግሎት ላይ የታዩ የሲስተም ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የለሁሉ አፈጻጸም በተመለከተ በ11/10/10 የቀረበ ኦዲት ሪፖርት መሰረት የውሃ፣ የመብራት እና የስልክ አገልግሎት ሰጪዎች ለክፍያ ፋይናንሻል የሚሰበሰብበትን ደረሰኝ ከላኩ በኃላ የተሸጠውንና ያልተሸጠውን ለድርጅቶቹ የሚያሳውቀው በኢሜል ተጠቅሞ ሲሆን የተገልጋይ ተቋማት (utilities) ክፍያዎች ደግሞ ወደ ባንክ የገባለቸውን በኢሜል ከተላከላቸው ጋር በማገናዘብ የሚከናወን በመሆኑ አንድ ደንበኛ በስህተት የአንድ ወር ክፍያ 2 ጊዜ ቢከፍል ሲስተሙ ሊይዘው አለመቻሉ ገልፀዋል፤
- ከሲስተሙ የሚወጣው ፕሪንት አውት ቀለሙ የጠፋ እና የማይታይ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ባሉ 34 የለሁሉ ማእከላት ህዳር 2009 በተደረገ ክትትል ስራ ሪፖርት በሁሉም ማዕከላት ዳታ የመናበብ ችግር በመኖሩ ደንበኞች በድጋሚ ክፍያ የሚከፍሉ መሆኑ እና በድጋሚ ስለመከፈሉ በሲስተሙ የሚታይበት እና የሚመለስበት ስርዓት አለመዘርጋቱ፤
- በገርጂ፣አጠና ተራ ፣18 ማዞሪያ፣አየር ጤና እና ለቡ ማእከላት የፕሪንተር ጥራት የሌለው በመሆኑ ፕሪንት አውቱ የሚጠፋ መሆኑ፤

- በቦሌ ሚሊኒየም፣ወሎሰፈር ካዛንችስ፣ ለገሀር፣ ስድስት ኪሎ እና አራት ኪሎ ተራ ማጠበቂያ ማሽን በስራ ላይ አለመዋል፤ በገርጂ ቦሌ፣ ሚካኤል፣ አጠና ተራ፣ 18 ማዞሪያ ተራ ማጠበቂያ ማሽን አለመኖር፣
- ቦሌ ሚሊኒየም ከሲስተምና ኔትዎርክ መቆራረጥ ጋር የተያያዘ ችግር ያለበት መሆኑ፣
- በሁሉም ማዕከላት የደረሰኝ የክፍያ መጠን ላይ በየወሩ ምን ያህል የገንዘብ መጠን ደንበኞች እንደሚከፍሉ በግልጽ የሚያሳይ መረጃ አለመኖር፣
- በ18 ማዞሪያ አዳዲስ ደንበኞች በማእከሉ በሚስተናገዱበት ወቅት መረጃው በሁሉም ማእከላት አለመላኩ፣
- ለቡ በቅሎ ቤት የትራፊክ ቅጣት ሲስተም መቋረጥና መዘግየት፣በገርጂ እና ጉርድ ሾላ የመብራት መለያ ቁጥር በመስሪያ ቤት ሲቀየር በማእከል ደረጃ መረጃው ባለመድረሱ ደንበኞች በድጋሚ የማረጋገጫ ደብዳቤ መጠየቅ፣
- በለገሀር፣ካዛንችስ፣ፈረንሳይ እና ስድስት ኪሎ ከ20-30 ደንበኞችን ካስተናገደ በኃላ ኮምፒተሮች stack ማድረጋቸው፣በቤተል ወይራ ደንበኞች የስልክ ክፍያ ከፈጸሙ በኃላ ወዲያውኑ የስልክ መስመሩ አለመከፈቱ፤
- በካሳንችስ እና ተክለኃይማኖት ማእከላት የጀኔሬተር አለመኖር የመብራት አገልግሎት በሚቋረጥበት ወቅት የደንበኞች መጉላላት መፈጠር፣
- በመቐለ ለሁሉ ክፍያ ማእከላት የደንበኞችን መረጃ ከማስታረቅና በየወቅቱ update የማድረግ ስራ ከወራት በላይ የሚቆይና ዓመት የሚፈጅም የውዝፍ ዳታ ማስታረቅ ስራ የተጠራቀመ መሆኑ፣
- እንዲሁም ለሁሉ ክፍያ ማእከላት አንዳንድ ጊዜ በአንዱ የአገልግሎት ማእከል የተመዘገበ ደንበኛ መረጃው በወቅቱ በሌሎች ማእከላት ሊገኝ አለመቻል በዚህም ምክንያት ደንበኞች በሚፈልጉት ወይም በአቅራቢያቸው የክፍያ ማእከላት መክፈል አለመቻሉ፤
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አገር አቀፍ የሆነ የአሽከርካሪዎች ዳታ ቤዝ አለመኖሩ ይህም የክፍለ አገር መንጃ ፍቃድ ያላቸው አሽከርካሪዎች እና አዲስ መንጃ ፈቃድ ያላቸው አሽከርካሪዎች ቅጣታቸውን በክፍለ ከተማ በሚገኙ ጽ/ቤቶች እንደሚከፍሉ በመሆኑ በለሁሉ ማዕከል አገልግሎት መስጠት አለመቻሉ፣

- የትራፊክ ቅጣት ደረሰኝ ላይ የተቀጣው ብር መጠን ሳይሆን የቅጣት ደረጃ የሚገለጽ መሆኑ፣ በተጨማሪም አሽከርካሪዎች የተቀጡበትን ደረሰኝ በተቀጡበት አካባቢ በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ በመስጠት መንጃ ፈቃዳቸውን የሚወስዱ በመሆኑ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ኤጅንሲው የቅጣት መጠኑን እና በክፍያ የተሰበሰበውን ገንዘብ መጠን የሚያመሳክርበት ስርአት አለመኖሩ፣

121. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ቴክኖሎጂ መቶ በመቶ ከስህተት የፀዳ ውጤት የለውም በየጊዜው ከሚታዩ ችግሮች መፍትሄ እየተሰጠው እያደገ የሚሄድ ችግሮች ሲመጡ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) ጋር በጋራ በሚደረግ ውይይት ለመፍታት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል ችግሩ የሚመጣው ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) የሚመጣ ዳታ እና በአንድ ወቅት ደግሞ ከኢትዮ ቴሌኮም / System integration/ ችግር የመጣና የተስተካከለ ነው ፡፡ ጉዳዩ ለስትሪንግ ኮሚቴ ቀርቦ ሲስተሙ ሙሉ በሙሉ ግልፅ እንዲደረግ ተብሎ በኢትዮ ቴሌኮም ተግባራዊ መደረግ ተጀምሯል፡፡ በሌሎች ተቋማት ግን በራሳቸው በኩል ማሟላት የሚገባቸው የቴክኖሎጂ ማበልፀግ ሂደቶችን እየተደረገ የሚፈታ ነው፡፡ እንዲሁም መብራት ጠፍቶ ሲበራ ሲስተሙ የራሱን ጤንነት ዲያጎኒስቲክ (Upgrading and self diagnosys) አድርጎ ሰለሚነሳ ከ20-30 ደቂቃ መዘግየቱ ይህ በዘርፉ የተለመደ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ሲስተም ኦዲት ለማድረግ እንዲተባበረን ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ተጠይቆ ሳይሰራ ቆይታል ብለዋል፡፡

122. በመሆኑም የኦዲት ቡድኑ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት ሲስተም ሶፍትዌር ኦዲት (system audit) በማካሄድ ከሲስተሙ የሚወጣው ሪፖርት ትክክለኛነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያረጋግጥበት ስርአት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት አፈፃፀምን በተመለከተ

123. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶች በአንድ ቦታ እንዲገኙ (one stop shop) በማድረግ የተቀናጀ የክፍያ ስርአት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

124. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው በUBS1 እና በUBS2 በተደረገው ውል መሰረት በአዲስ አበባ፣መቀሌ እና

በባህርዳር ከተሞች ማህበረሰቡ የተለያዩ ክፍያዎችን (ውሃ፣መብራት፣ስልክ) በአንድ ቦታ እንዲከፈል እና ማህበረሰቡ እንዲጠቀም ለማስቻል ሲባል የተዘረጋ ቢሆንም በአተገባበር ላይ ግን በአንድ ቦታ አገልግሎት እንዲሰጥ እየተደረገ አለመሆኑ፤ ማለትም ኢትዮ ቴሌኮም ትልልቅ ኢንዳስትሪዎች፣ ኢንባሲዎች እና ሌሎች ትልልቅ ተቋማትን የሚያስከፍለው በቴሌ ሾፕ መሆኑ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከፍተኛ ሀይል ተጠቃሚ ደንበኞችን ኢንዱስትሪዎችን፣ ትላልቅ ተቋማትን እና የቅድመ ክፍያ ቆጣሪዎች አገልግሎት በራሱ ደንበኞች አገልግሎት እንደሚያስከፍል በመሆኑ አገልግሎቱ በአንድ መስኮት እየተሰጠ አለመሆኑ ታውቋል፡፤

125. እንዲሁም በUBS2 ውል መሰረት አዋሳ፣ አዳማ፣መቀሌ እና በባህርዳር ከተሞች (ውሃ፣መብራት፣ስልክ) በተቀናጀ መልኩ አገልግሎት ለመስጠት ቢዋዋልም፤ አገልግሎቱ በአዋሳ እና አዳማ ከተሞች አለመጀመሩ፤ በተጨማሪም በመቐለ እና በባህርዳር ከተሞች የውሃ ክፍያ የአገልግሎት በለሁሉ የክፍያ ማዕከል የማይከፈል መሆኑ ታውቋል፡፡

126. በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ለኢትዮ ቴሌኮም ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደታየው በአዲስ አበባ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ደንበኞች አገልግሎት የክፍያ ማዕከላት ክፍያ የሚሰበስቡ መሆኑ እነሱም ትልልቅ ተቋማት፣ ኢንዱስትሪዎች፣ መከላከያ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቶች እና የመሳሰሉት ከፍተኛ ሃይል ተጠቃሚዎች ደንበኞች እና የቅድመ ክፍያ ካርድ አገልግሎት የሚጠቀሙ በአማካኝ እስከ 488,000 የሚደርሱ በደንበኞች በቀጥታ ክፍያዎችን እንደሚሰበስቡ መሆኑ፤ እንዲሁም ኢትዮ ቴሌኮም በቴሌ ሾፕ ማዕከል የሚከፍሉ የደንቦኞች ብዛት 109,043 መሆኑ፤ በተጨማሪም አዲስ መንጃ ፈቃድ ያላቸው አሽከርካሪዎች የመጀመሪያ ቅጣት በክፍለ ከተማ እንደሚከፍሉ ታውቋል፡፡

127. ከላይ በተገለፀው መሰረት በአዲስ አበባ ሪጅን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ወደ ለሁሉ ማዕከል የገቡት 320,000 ደንበኞች ሲሆኑ ያልገቡት ደግሞ 488,000 መሆናቸው እንዲሁም በኢትዮ ቴሌ ወደለሁሉ ማዕከል የገቡ 250,000 ደንበኞች ሲሆኑ 109,000 በራሳቸው ማዕከል የሚሰበስቡ በመሆኑ የተቀናጀ የክፍያ ሥርዓት በአንድ ማዕከል ለመስጠት አለመቻሉ ታውቋል፡፡

128. ስለሁኔታው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በUBS1 በተደረገው ውል መሰረት በአዲስ አበባ ማህበረሰቡ የተለያዩ ክፍያዎችን (ውሃ፣መብራት፣ስልክ) በአንድ ቦታ እንዲከፍል እና ማህበረሰቡ እንዲጠቀም የሚል ቢሆንም ኢትዮ ቴሌኮም እና የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት በራሳቸው ማዕከል ክፍያ ይሰበስባሉ ብለዋል፡፡

129. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት በውሉ መሰረት የ(one stop shop) አገልግሎት ባለመዘርጋቱ ማህበረሰሁ በአንድ ቦታ እንዳይከፍል እና የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዳያገኝ ከማድረጉም በላይ በለሁሉ ፕሮጀክት የተለያዩ ክፍያዎች ማቀናጀት/ዩኒፋይድ/ ለማድረግ የታቀደው አላማ እንዳይሳካ አድርጓል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ

130. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለሁሉ የክፍያ ማዕከላት የሚሰጠው አገልግሎት በውሉ (service level agreement) መሰረት ስለ መሆኑ ቋሚ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

131. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክፍያ ማዕከላት የሚደርገውን ክትትል እና ድጋፍ ዕቅድ መሰረት አለመሆኑ፣ የሚሰጡ ድጋፍና ክትትል ወጥ በሆነ መልኩ አለመደረጉ እና ግብረ መልስ የሚሰጥበት ስርዓት አለመኖሩ ታውቋል፡፡

132. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ለኢትዮ ቴሌኮም፣ ለአዲስ አበባ ውሃ እና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ባለስልጣን ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለመጠይቅ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለሁሉ ማዕከላት ድጋፍና ክትትል በማድረግና ግብረ መልስ ስለመስጠታቸው እንደማያውቁ ገልፀው፤ በ(service level agreement) ውል መሰረት በለሁሉ ማዕከላት አገልግሎት ለመስጠት የተቀመጠው ሰዓት ከ15 ደቂቃ ያነሰ ቢሆንም ለሰዓታት በወረፋ የሚጠብቁ ተገልጋዮች ያሉ ሲሆን፤ በዚህ ጉዳይ ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማህረብ ይህ በተመለከተ ተቀዋቶ እንደማያውቅ ገልፀዋል፡፡

ስዕል 1 በለገሃር ለሁሉ ማዕከል ክፍያ ለመፈፀም ወረፋ የሚጠብቁ ደንበኞች

133. በተጨማሪም በውል UBS 1&2 አባሪ 2 ገጽ 6 አገልግሎት አቅራቢ ድርጅትን ኃላፊነቶች ሲገልጽ ISO17799 (Information security management) ማረጋገጫ በ12 ወር እንድያገኝ ቢቀመጥም በሚኒስቴር መ/ቤ ክትትል አለመደረጉ፣

134. ለኦዲቱ በናሙና ለተመረጡ 17 የክፍያ ማዕከላት ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች በቀረበ ቃለመጠይቅ በሰጡት ምላሽ እና በአካል በተደረገው ምልከታ የሚከተሉት ታይተዋል፡-

- በአዲስ አበባ አራዳ ክፍለ ከተማ የለሁሉ ማዕከል የመብራት መቆራረጥ መኖሩ በአዲስ አበባ ቤተል አካባቢ የለሁሉ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የደንበኞች ቅሬታ መኖሩ፤
- በሁሉም ማዕከላት የደንበኞችን ወረፋ/ተራ የሚስተባብሩ ባለሞያዎች በቂ አለመሆን፣ ወረፋ ለመጠበቂያ የሚሆን በቂ ማረፊያና መጠለያ ያለመኖር
- በሁሉም ማአከላት የውጪ ማስታወቂያ ሰሌዳ ለእይታ መደብዘዝና ጥራቱን ያልጠበቀ መሆን፣
- 9 የክፍያ ማዕከላት ተራ መጠበቅያ ማሽን እንደሌላቸው 8 የክፍያ ማዕከላት ተራ መጠበቅያ ማሽን ቢኖራቸውም አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤

- በ16 የክፍያ ማዕከላት እያገለገሉ ያሉ ፕሪንተሮች ለብዙ አመታት ያገለገሉና ያረጁ በመሆኑ ፕሪንተሩ የሚያትመው ደረሰኝ ደብዛዛ እና በቀላሉ ለመረዳት የማያስችል የጥራት ችግር መኖሩ ፤
- ደንበኞች ክፍያ እንደፈፀሙ ዳታው ከሲስተሙ ላይ ክሊር ስለማይደረግ ድጋሚ የሚከፈልበት አጋጣሚ መኖሩ፣ እና ድጋሚ ስለመክፈላቸው ከግለሰቦች ጥያቄ ካልመጣ በስተቀር በሲስተም የሚታይበት ሁኔታ አለመኖሩ፣
- በመብራት ሲጠፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አውቶማቲክ ጀንሬተር አለመኖሩ

135. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ወቅት ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎቱ በውሉ (service level agreement) መሰረት እየተሰጠ ስለመሆኑ በየጊዜው ሳምፕል መርጦ እንደሚከታተል ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ISO17799 (Information security management) ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አለማግኘቱ ገልፀዋል፡፡

136. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ክፍያ ስርዓት በክፍያ ማዕከላት የሚሰጠው አገልግሎት በውሉ (service level agreement) መሰረት ስለመሆኑን ቋሚ ክትትል እና ድጋፍ ባለማድረጉ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና ማህበረሰቡ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ማግኘት እንዳይችሉ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡እንዲሁም ግብረ መልስ የሚሰጥበት አሰራር ባለመኖሩ ስራው ከነበረበት እንዳይሻሻል አድርጓል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደንበኞች አገልግሎት

የእርካታ ጥናት ማከናወኑን በተመለከተ

137. መስሪያ ቤቱ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና ከማህበረሰቡ የደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት ሊያከናውን እና ቅሬታ የሚፈታበት ስርአት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

138. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና ከማህበረሰቡ

የደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት ያላደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም በአገልግሎት ወቅት የሚፈጠሩ ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚያስችል ስርአት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

139. እንዲሁም ለአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አፈጻፀሙን በተመለከተ የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት የአፈፃፀም ብቃት የህብረተሰቡንና ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት እንዳላጠና እና እንዳልተሳተፉ ገልፀዋል፡፡

140. በተጨማሪም ለኢትዮ ቴሌኮም ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክፍያ ፋይናንሻል ዳታ በ24 ሰዓት እና ጥሬ ገንዘብ በ48 ሰዓት ባለመግባቱ በተደረገው ውይይት ቅሬታ ቢያቀርቡም መፍትሄ እንዳልተሰጣቸው ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በለሁሉ ማዕከላት የሚሰጥ አገልግሎት የደንበኛ አያያዝ የተሻለ እንዳልሆነ ገልፀው ነገር ግን በ8586 የስልክ መስመር ገንዘብ የሚከፈልበት የተገልጋይ ደንበኛ ቅሬታ የሚቀርብበት ቢሆንም፤ ነገር ግን ለቅሬታ ነፃ የስልክ መስመር መኖር እንደነበረበት ገልፀዋል፡፡

141. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ለናሙና ከተመረጡ 17 የክፍያ ማዕከላት ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች በተደረገ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከማህበረሰቡ የሚሰበሰቡ ቅሬታዎች ተሰብስበው ወደ ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር እንደሚልኩ ሲሆን በለሁሉ ማዕከላት ቅሬታ የሚፈታ ኦፊሰር አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

142. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ይህ ጉዳይ የአገልግሎት ሰጪ ድርሻ መሆኑንና በእነሱ በኩል ክፍያ ፋ/ቴ/ኃ/የተ/የግ/ማ ያጠናውን የደሰሳ ጥናት እንደገመገሙ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የደንበኞች እርካታ ጥናት አለመደረጉን ገልፀዋል፡፡

143. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና ከማህበረሰቡ የደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት አለማካናወኑ እንዲሆም ቅሬታ የሚፈታበት ስርዓት ባለመዘርጋቱ አፈፃፀሙ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች መፍትሄ እንዳይሰጣቸው በማድረግ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዳያሰጥ ተፅዕኖ ይፈፅራል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ

144. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለሁሉ ኮንትራት ሰነድ መሰረት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና አገልግሎቱን ከሚሰጠው የግል ድርጅት የተውጣጣ ኮሚቴ እና የስራ አስፈጻሚ ቡድን በማቋቋም ወደ ስራ ሊገባ ይገባል፡፡

145. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው መሰረት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና አገልግሎቱን ከሚሰጠው የግል ድርጅት የተውጣጣ ኮሚቴ እና የስራ አስፈጻሚ ቡድን የተቋቋመ ቢሆንም በቀጣይነት ስራ እየሰራ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

146. በኦዲቱ ወቅት ለክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጅ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ መልስ ሲሰጡ በፕሮጀክት/execution/ ጊዜ በየሳምንቱ እና ተደጋጋሚ ስብሰባዎችን እና ግምገማዎች የነበሩ ሲሆን ፕሮጀክቱ ተግባራዊ /operational/ ከሆነ በኋላ ግን የግንኙነት ጊዜው በተራራቀ ሁኔታ መሆኑን እና በዚህ ምክንያት ለሚፈጠሩ ችግሮች በጊዜ መፍትሄ ማግኝት አለመቻሉ ለምሳሌ /የቢሮ ኪራይ ክፍያ በለገሃር መድን መጠየቁ፣ የቢሮ ልቀቁ ጥያቄ ሳር ቤት፣ የካ ሃያ ሁለት፣መገናኛ፣ሜክስኮ መጠየቃቸው ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

147. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የፕሮጀክቱ መጀመሪያ ሰሞን ከሶስቱ ተገልጋይ ተቋማት (utilities) ከግል ድርጅቱና ከሚኒስተር መስሪያ ቤቱ የተውጣጣ ኮሚቴ የነበረ ቢሆንም በተቋማት የነበሩ የበላይ አመራር መለዋወጥ እና በተቋማት የነበሩ የበላይ ኃላፊዎች እንዲሁም ባለሙያዎች ስራ መልቀቅ ምክንያት መቀጠል አልተቻለም ብለዋል፡፡፡

148. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ አስፈፃሚ ቡድን በማቋቋም በቅንጅት እንዲሰሩ ባለመደረጉ ችግሮች በየጊዜው እየተገመገሙ ምላሽ እንዳያገኙ በማድረግ ውጤታማና ቀጣይነት ያለው ስራ እንዳይሰራ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡

ሚ/ር መስሪያቤቱ የውል ጊዜው ሲጠናቀቅ

ስራውን መረከቡን በተመለከተ

149. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለሁሉ ኮንትራት ውል መሰረት የኮንትራት ጊዜው ሲጠናቀቅ ስራውን በመረከብ አገልግሎቱን ሊያስቀጥል ይገባል፡፡

150. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው ለአዲስ አበባ እ.ኤ.አ ጁን 2011 በወጣው ጨረታ ያሸነፈው ግሎባል ኮንፒውቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተባለው ድርጅት ከ3 አመት ከ6 ወር በኋላ በ እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 2015 ስራውን ማስረከብ ቢኖርበትም ያላስረከበ መሆኑ እና ለአንድ አመት ባልተራዘመ ውል ሲሰራ ቆይቶ እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 2016 የውል ማሻሻያ በማድረግ ኮንትራቱን ለሁለት አመት የተራዘመ መሆኑ፤ እንዲሁም እ.ኤ.አ በ2017 ጨረታ የወጣ ቢሆንም እንደገና ውሉ ለአንድ አመት በማራዘም ባጠቃላይ ውሉ ለ3 አመት መራዘሙ ታውቋል፡፡

151. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በመንግስት በኩል የክፍያ ማዕከላት የማቅረብ ግዴታ ባለመሟላቱ ምክንያት ጊዜውን ጠብቆ አልተጀመረም ሆኖም ምንም እንኳን ወቅቱን ጠብቆ ስራ አለመጀመሩ ከመንግስት የበለጠ ኩፍኛ የሚጎዳው ድርጅቱ ቢሆንም ስራው በይፋ ከተጀመረበት ጀምሮ የሚቆጠር ጊዜ ተሰርቶ ስያልቅ በደንበኛ ቁጥር ማነስ ምክንያት እና በኃላም ቀድሞ በነበሩ አመራሮች የሚመራ አዲስ የጨረታ ሂደት አልቆ አሸናፊው የተለየ ቢሆንም በመካከሉ በተደረገ የአደረጃጀት የማስተካከል ሂደት ቀድሞ በነበሩ አመራሮች በሙሉ በአዳዲስ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በመተካታቸው እና አመራረቹ ፕሮጀክት ለመምራት ጊዜ ባለማግኘታቸው እንዲሁም በጠቀስዋቸው ሌሎች ምክንያቶች አሸናፊ ድርጅት ጋር አዲስ ውል ሳይፈፀም ለአንድ አመት እንዲራዘም መደረጉን ገልፀዋል፡፡

152. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውል መሰረት UBS 1 የኮንትራት ጊዜው ሲጠናቀቅ ስራውን መረከብ ቢኖርበትም አለመረከቡ ስራውን ሌላ ጨረታ ወጥቶ እንዳይቀጥል በማድረግ ስራው ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዳይኖር እና በሞኖፖሊ እንደተያዘ እንዲቀጥል አድርጎታል፡፡

ክፍል ሶስት

መደምደሚያ

153. በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥና አፈፃፀም ዙሪያ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

154. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት በሀገሪቱ ሊኖር ስለሚችለው የተቀናጀ ክፍያ ስርዓትን የተመለከተ የአዋጭነት ጥናት ያላጠና መሆኑ፤

155. የተቀናጀ ክፍያ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት የተገልጋይ ተቋማት (utilities) የፍላጎት መግለጫ (Need assessment) በመስራት ስምምነትን መሰረት ባደረገ መልኩ አለመጀመሩ፤

156. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት (UBS 1) ባወጣ ጨረታ ላይ ከድርጅቱ ጋር ድርድር በማድረግ የዋጋ ለውጥ ማድረጉ፣

157. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግል/ማህበር ጋር ያደረገው ውል በግዥ ሰነዱ (Request for proposal (RFP)) መሰረት አለመሆኑ፣

158. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ ክፍያ አገልግሎትን ከፖሊስው ውጭ ከግል ድርጅቱ ጋር ያደረገው ውል አባሪ 1 ገጽ 3 ላይ በአገልግሎቱ የተመረጡ የንግዱ ዘርፍ ለዜጎች የሚሰጠውን አገልግሎት ወደ ለሁሉ አገልግሎት መግባት እንደሚችሉ (ፖሊሲውን ባልተከተለ ሁኔታ) በመግለፅና በማፅደቅ ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማህበር (የግል ዘርፍ) ከአገር አቋራጭ አውቶብሶች ባለንብረቶች(የግል ዘርፍ) ጋር በመዋዋል የአገር አቋራጭ አውቶብሶች ትኬት በለሁሉ ማእከላት እየተሸጠ መሆኑ፣

159. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥን በተመለከተ አማካሪ ድርጅት ሲቀጥር በጨረታ ህጉ መሰረት አለመሆኑ፣

160. በጨረታ ያሸነፈው ድርጅት ውል ላይ በተቀመጠው ቀን መሰረት ስራ አለመጀመሩ፣

161. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ውል መሰረት ከቀረጥ ነጻ የገቡ እቃዎችን የውል ጊዜው ሲጠናቀቅ ለመረከብ በሚያመች መልኩ ስለመያዛቸው ክትትል አለመደረጉ እና በየአመቱ ቆጠራ አለመደረጉ፣

162. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፈው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ባደረገው ውል መሰረት የፋይናንስና የክፍያ ሥርዓቱን የሚከታተልበት ስርአት ቢዘረጋም ተግባራዊ አለመደረጉ

163. የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት የሚያከናውነው የግል ድርጅት የሂሳብ ኦዲት ሪፖርት በማስደረግ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በየአመቱ የሚያቀርብበት ስርዓት አለመዘርጋቱ፣

164. የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት ሲስተም ሶፍትዌር ኦዲት (system audit) በማካሄድ ከሲስተሙ የሚወጣው ሪፖርት ትክክለኛነት እንደማያረጋግጥ፣

165. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ሰነድ ውል መሰረት 41 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በአዲስ አበባ እንዲሁም 14 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በክልል ከተሞች እንዲከፈቱ በማድረግ አገልግሎቱን በተቀላጠፈ መንገድ መስጠት የሚል ቢሆንም በአዲስ አበባ 34 ማዕከላት በክልሎች 8 ማዕከላት ብቻ መከፈታቸው፣

166. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶች በአንድ ቦታ እንዲገኙ (one stop shop) በማድረግ የተቀናጀ የክፍያ ስርአት የተዘረጋ ቢሆንም ተግባራዊ አለማድረጉ፣

167. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ ወደ ለሁሉ አገልግሎት የሚገቡ አዳዲስ ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ በጥናት መሰረት እንደማይወሰን፣

168. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ክፍያ ስርዓት የክፍያ ማዕከላት የሚሰጠው አገልግሎት በውሉ (service level agreement) መሰረት መሆኑን ቋሚ ክትትል እና ድጋፍ አለማድረጉ እና ግብረ-መልስ አለመስጠቱ፣

169. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለለሁሉ አገልግሎት የሚውሉ ንብረቶችን ዋስትና መድህን (Insurance) መግባታቸውን ቁጥጥር አለማድረጉ፣

170. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለሁሉ ኮንትራት ሰነድ መሰረት ከተገልጋይ ተቋማት፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱና አገልግሎቱን ከሚሰጠው የግል ድርጅት የተውጣጣ ኮሚቴ እና የስራ አስፈጻሚ ቡድን ቢቋቋምም ቀጣይነት ባለው መልኩ እየሰሩ አለመሆኑ፣

171. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት በተመለከተ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፤

172. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ ክፍያ ስርአትን አገልግሎትን በተመለከተ ለባለ ድርሻ አካላትና ተገልጋይ ተቋማት (utilities) ወርክ ሾፕ እንደማያዘጋጅ እንዲሁም ስልጠና አለመስጠቱ፣

173. መስሪያ ቤቱ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና ከማህበረሰቡ የደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት አለማከናወኑ እና ቅሬታ የሚፈታበት ስርአት ተግባራዊ አለመደረጉ፤

174. በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብለው የታመነባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች

175. በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥና አፈፃፀም በተመለከተ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወንና በተለያዩ ለህብረተሰቡ የሚሰጡ አገግሎቶች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በማዘመን ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ፈጣንና ተደራሽ አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም በቀጣይ በሚከናወኑ የስራ እንቅስቃሴዎች ላይ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

176. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት በሀገሪቱ የሚኖረውን የተቀናጀ ክፍያ ስርዓት የተመለከተ የአዋጭነት ጥናት ማድረግ አለበት፡፡

177. አገልግሎቱ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ቢሰራ ገቢው ለመንግስት እንዲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን ለግል ሴክተር ለጨረታ ከማቅረቡ በፊት በመንግስት ተቋማት አገልግሎቱን መስጠት እንደማይችል ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

178. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ሥርዓትን ስለመመስረት ከተገልጋይ ተቋማት (Utilities) የፍላጎት መግለጫ (Need assessment) በመስራት ስምምነትን መሰረት ባደረገ መልኩ ሊሰራ ይገባል፡፡

179. ህግን የተከተለ አሰራር እንዲኖር ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አሸናፊው ተጫራች ጋር ዋጋ እና ከዋጋ ጋር ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች የሚያደርገው ድርድር በግዥ ህጉ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

180. አነስተኛ የጨረታ ዋጋ ያቀረበ ተወዳዳሪ ለመለየት እንዲቻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን ግዢ ጨረታ ከማውጣቱ በፊት ተገልጋይ ተቋማት (utilities) ያላቸውን የደንበኛ ብዛት ታሳቢ ያደረገ አማካኝ የትራንዛክሽን ዋጋ ሊወስን ይገባል፡፡

181. ወጥ የሆነ እና ህግን የተከተለ አሰራር እንዲኖር ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ጨረታ ካሸነፈው ድርጅት ጋር የሚያደርገውን ውል በግዥ ሰነዱ (Request for proposal) መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

182. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥን በተመለከተ አማካሪ ድርጅት ሲቀጥር በጨረታ ህጉ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

183. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፊው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ያደረገው ውል ተገልጋይ ተቋማት (utilities) የሚሰበስቡትን የአገልግሎት ክፍያ በትክክል የሚያስተዳድሩ ስለመሆኑ ኦዲት ወቅት ግልፅ አሰራር እንደሌለ ለማወቅ ችለናል እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጨረታውን ካሸነፊው ግሎባል ኮንፒቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ባደረገው ውል መሰረት የፋይናንስና የክፍያ ሥርዓቱን የሚከታተልበት ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በቀጣይ የፋይናንሻል እና የሲስተም ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡

184. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ ወደ ለሁሉ አገልግሎት የሚገቡ አዳዲስ ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ በጥናት መሰረት መወሰን አለበት፡፡

185. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጨረታ ያሸነፊው ድርጅት ውል ላይ በተቀመጠው ቀን መሰረት ስራ ማስጀመር እና ውል ሲዋዋል ስራ የሚጀመርበት ቀን መገለፅ ይኖርበታል፡፡

186. ለለሁሉ አገልግሎት ተብለው የገቡ ዕቃዎች ብዛታቸው እንዲታወቅና ለተባለላቸው አላማ እንዲውሉ እንዲሁም ውሉ ሲጠናቀቅ ንብረቶቹ ለመረከብ አመቺ እንዲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ውል መሰረት ከቀረጥ ነጻ የገቡ እቃዎችን የውል ጊዜው ሲጠናቀቅ ለመረከብ በሚያመች መልኩ ስለመያዛቸው ሊከታተል እና በየአመቱ ቆጠራ ሊያደርግ ይገባል፡፡

187. ለደንበኞች ጊዜ ቆጣቢ እና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ውል መሰረት ያቀረባቸው ንብረቶችና ቢሮዎች ለታሰበላቸው አገልግሎት ብቻ ስለመዋላቸው ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

188. የግል ድርጅት የሂሳብ ኦዲት ሪፖርት በማስደረግ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በየአመቱ የሚያቀርብበት ስርዓት ሊኖር ያገባል፡፡

189. የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት ሲስተም ሶፍትዌር ኦዲት (system audit) በማካሄድ ከሲስተሙ የሚወጣው ሪፖርት ትክክለኛነት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚያረጋግጥበት ስርአት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

190. የተለያዩ ክፍያዎች በአንድ መስኮት እንዲሰጡ እና ማህበረሰቡ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለማግኘት እንዲችል ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ሰነድ መሰረት የክፍያ ማዕከላት መክፈት ይኖርበታል፡፡

191. ማህበረሰቡ የተለያዩ አገልግሎቶች በአንድ ቦታ እንዲከፍል ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶች በአንድ ቦታ እንዲገኙ (one stop shop) በማድረግ የተቀናጀ የክፍያ ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

192. ማህበረሰቡ የተቀላጠፈ እና ጥራት ያለው አገልግሎት እንድያገኝ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለሁሉ ክፍያ ማዕከላት የሚሰጠው አገልግሎት በውሉ (service level agreement) መሰረት መሆኑን ቋሚ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም ክትትል እና ድጋፍ በዕቅድ የተካተተ ሊሆን ይገባል፡፡

193. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለለሁሉ አገልግሎት የሚውሉ ንብረቶችን የኮንትራት ጊዜው ሲጠናቀቅ ለማስረከብ እንዲቻል አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት ዋስትና መድህን (Insurance) እንዲያስገባቸው ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

194. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለሁሉ ኮንትራት ሰነድ መሰረት ከተገልጋይ ተቋማት (utilities ከሚኒስቴር መ/ቤቱና አገልግሎቱን ከሚሰጠው የግል ድርጅት የተውጣጣ ኮሚቴ እና የስራ አስፈጻሚ ቡድን በማቋቋም እና በማስተባበር ወደ ስራ ሊገባ እና በቀጣይነት ሊሰራበት ይገባል፡፡

195. በተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና በአገልግሎት አቅራቢ ድርጅት እንዲሁም በማህበረሰቡ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ለመፍታት መስሪያ ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት በተመለከተ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

196. የማህበረሰቡን እና የተገልጋይ ተቋማትን (utilities) የደንበኞች እርካታ ለመረዳት እና የደንበኞችን ቅሬታ ለመፍታት እንዲያስችል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተገልጋይ ተቋማት (utilities) እና ከማህበረሰቡ የደንበኞች እርካታን የዳሰሳ ጥናት የሚደረግበትን ስርአት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች፣ አመራሮችና ሰራተኞች በሙሉ እንዲሁም ቃለ መጠይቅ ላቀረብንላቸው ተገልጋይ ተቋማት

(utilities) እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲሁም አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች በወቅቱ ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

ኦዲት ተደራጊ መ/ቤት፡-የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

የኦዲት አካባቢ፡-የለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥና አገልግሎት አፈጻጸምን በተመለከተ

ተ.ቁ	የትኩረት አቅጣጫ	መመዘኛ መስፈርት
1	የለሁሉ ኮንትራት አሠጣጥ የግዥ ህጉን የተከተለ፣ ውልን መሰረት ያደረገ እና የተሻሻለ አገልግሎት ለተጠቃሚው መስጠት በሚያስችል መልኩ ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መልኩ የተከናወነ መሆኑን መገምገም፤	1.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት በሀገሪቱ የሚኖረውን የተቀናጀ ክፍያ ስረዓት የተመለከተ የአዋጭነት ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- (Guidelines to implement PPP Projects) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የመንግስት እና የግል አጋርነት ጋይድ ላይን ገጽ 35
		2.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን ለግል ሴክተር ለጨረታ ከማቅረቡ በፊት በመንግስት ተቋማት አገልግሎቱን መስጠት እንደማይችል ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- ብሄራዊ ኢንፎርሜሽን እና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነሀሴ 2009 ገፅ 13 እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የመንግስት እና የግል አጋርነት ጋይድ ላይን ገጽ 14
		3.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ከመፈፀሙ በፊት በግዢ እቅድ ሊያካትትና በእቅዱ መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ሊያከናውን ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 22 ንኡስ አንቀጽ 1
		4. የተቀናጀ የክፍያ ሥርዓትን ስለመመስረት ከአገልግሎት ሰጭ ተቋማት (Utilities) የፍላጎት መግለጫ (Need assessment) በመስራት ስምምነትን መሰረት ባደረገ መልኩ ሊሰራ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ
		5.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት (UBS 1,UBS 2 & UBS3) ጨረታ ከመውጣቱ በፊት በየትኛውን የጨረታ ዘዴ መጠቀም እንደሚኖርበት በምክንያቶች ላይ ተደግፎ ሊመርጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 1 ረ
		6.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት(UBS 1,UBS 2 & UBS 3) በተመለከተ የግዥ ሂደቶችን የሚያሳዩ ማስረጃዎች በአግባቡ ሊይዝ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 1
		7.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት (UBS 1,UBS 2 & UBS 3) አሸናፊው ተጫራች ጋር ዋጋ እና ከዋጋ ጋር ግንኙነት ባላቸው

		ጉዳዮች የሚያደርገው ድርድር በግዥ ህጉ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 45 ንኡስ አንቀጽ 2 የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 58 ንኡስ አንቀጽ 7
		8.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራትን ግዢ ጨረታ ከማውጣቱ በፊት ተገልጋይ ተቋማት(utilities) ያላቸውን የደንበኛ ብዛት ታሳቢ ያደረገ አማካኝ የትራንዛክሽን ዋጋ ሊወስን ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የፌደራል መንግስት ግዢ አፈጻጸም ማንዋል ህምሌ 2002 ገጽ 101
		9.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ጨረታ ካሸነፈው ድርጅት ጋር የሚያደርገውን ውል የግዥ ሰነዱን መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የግዥ ሰነድ እና የውል ሰነድ
		10.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ጨረታውን ካሸነፈው ድርጅት ጋር ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች የያዘ ውል በማዘጋጀት ሊፈራረም ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 46 ንኡስ አንቀጽ 2
		11.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥን በተመለከተ አማካሪ ድርጅት ሲቀጥር በጨረታ ህጉ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 3 ንኡስ አንቀጽ 1
		12.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ጨረታ ካሸነፈው ድርጅት ጋር የሚዋዋልበት የውል ሰነድ የሚኒስቴር መ/ቤቱን፣ ተገልጋይ ተቋማት(utilities)ንና የተጠቃሚውን ማህበረሰብ ጥቅም ያሰጠበቀ አድርጎ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ብሄራዊ ኢንፎርሜሽን እና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነሀሴ 2009 ገፅ 13 እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የመንግስት እና የግል አጋርነት ጋይድ ላይን ገጽ 36
		13.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለሁሉ ኮንትራት ውል መሰረት የኮንትራት ጊዜው ሲጠናቀቅ ስራውን መረከብ አለበት፡፡ ምንጭ፡-/ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል(Unified Billing System PPP contrat) ገጽ I እና ii የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የመንግስት እና የግል አጋርነት ጋይድ ላይን ገጽ 86
		14.በጨረታ ያሸነፈው ድርጅት ውል ላይ በተቀመጠው ቀን መሰረት ስራ መጀመር አለበት፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል ገጽ 6
		15. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የክፍያ ስርአት ለማከናወን የሚያስችል አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ (guideline) ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የኢ.መንግስት አዲስ የስራ ሂደት ቀረጻ ሰነድ(ቢ.ፒ አር) ግንቦት 2003 ዓ.ም ገጽ 16 እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የመንግስት እና የግል አጋርነት ጋይድ ላይን ገጽ 87-108 እና

		ብሄራዊ ኢንፎርሜሽን እና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነሀሴ 2009 ገፅ 14
		16.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ውል መሰረት ከቀረጥ ነጻ የገቡ እቃዎችን የውል ጊዜው ሲጠናቀቅ ለመረከብ በሚያመች መልኩ ስለመያዛቸው ሊከታተል እና በየአመቱ ቆጠራ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የፌደራል መንግስት ግዢ አፈጻጸም ማንዋል ሀምሌ 2002 ገጽ 288
		17.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ውል መሰረት ያቀረባቸው ንብረቶችና ቢሮዎች ለታሰበላቸው አገልግሎት ብቻ ስለመዋላቸው ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል አንቀፅ 8 ገጽ 8
2	የለሁሉ ኮንትራት አፈጻጸም የአገልግሎቱን በደንበኞች የስምምነት ሰነድ (service level aggrement) መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን መገምገም፣	18.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት የታሰበለትን የተቀናጀ የክፍያ ስርአት መሰረት እየተከናወነ ስለመሆኑ በየጊዜው ፋይናንሻል ስርአቱንና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱ ጥናት በማድረግ የኮንትራቱን አፈጻጸም ሊገመግም ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል አባሪ 2 ገጽ 2 እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የመንግስት እና የግል አጋርነት ጋይድ ላይን ገጽ 49
		19.የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት የሚያከናውነው የግል ድርጅት የሂሳብ ኦዲት ሪፖርት በማስደረግ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በየአመቱ የሚያቀርብበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የመንግስት እና የግል አጋርነት ጋይድ ላይን ገጽ 49
		20.የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት ሲስተም ሶፍትዌር ኦዲት (system audit) በማካሄድ ከሲስተሙ የሚወጣው ሪፖርት ትክክለኛነት ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል አባሪ 2 ገጽ 2
		21.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት ሰነድ መሰረት 41 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በአዲስ አበባ እንዲሁም 14 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በክልል ከተሞች እንዲከፈቱ በማድረግ አገልግሎቱን በተቀላጠፈ መንገድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል አንቀፅ 5 ገጽ 6 አንቀፅ 8 ገፅ 9
		22.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶች በአንድ ቦታ እንዲገኙ (one stop shop) በማድረግ የተቀናጀ የክፍያ ስርአት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል ገጽ i

		23.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ክፍያ ስርዓት የክፍያ ማዕከላት የሚሰጠው አገልግሎት በውሉ (service level agreement) መሰረት መሆኑን ቋሚ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል ገጽ I1 የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የመንግስት እና የግል አጋርነት ጋይድ ላይን ገጽ 78/80
		24.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለለሁሉ አገልግሎት የሚውሉ ንብረቶችን ዋስትና መድህን (Insurance) መግባታቸውን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል አንቀፅ 8 ገፅ 8
3	ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለለሁል አገልግሎት የሚያደርገውን ድጋፍ ክትትል፣ የመረጃ ልውውጥና የመረጃ አያያዝ እና ቅንጅታዊ አሰራርን መገምገም፡	25.በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማኔጅመንት አባላት የሚደረጉ ስብሰባዎች በቃለ ጉባኤ ሊይዝ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ
		26.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በለሁሉ ኮንትራት ሰነድ መሰረት ከአገልግሎት ሠጪ ተቋማት፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱና አገልግሎቱን ከሚሰጠው የግል ድርጅት የተውጣጣ ኮሚቴ እና የስራ አስፈጻሚ ቡድን በማቋቋም ወደስራ ሊገባ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል አባሪ 6 ገጽ 1-3 እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የመንግስት እና የግል አጋርነት ጋይድ ላይን ገጽ 84/85
		27.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት በተመለከተ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡ ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ
		28.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የለሁሉ ኮንትራት አገልግሎት ከሚሰጠው የግል ድርጅት ተከታታይነት ባለው መልኩ ሪፖርት ሊቀበል ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል አባሪ 8 ገጽ 3 እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ የግል የመንግስት አጋርነት ጋይድ ላይን ገጽ 78
		29.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ ክፍያ ስርአትን አገልግሎትን በተመለከተ ለባለ ድርሻ አካላትና ተገልጋይ ተቋማት(utilities) ወርክ ሾፕ ሊያዘጋጅና ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ዩኒፋይድ ቢሊንግ ሲስተም የመንግስት እና የግል አጋርነት ውል አንቀጽ 8 ገጽ 9
		30.መስሪያ ቤቱ ከተገልጋይ ተቋማት(utilities) እና ከማህበረሰቡ የደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት ሊያከናውን እና ቅሬታ የሚፈታበት ስርአት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የኢ.መንግስት አዲስ የስራ ሂደት ቀረጻ ሰነድ(ቢ.ፒ አር) ግንቦት 2003 ዓ.ም ገጽ 16፣33 እና 44